
# ሐመር

## ኢየሱስ ወደ ሰርግ ቤት ተጠራ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሄደ።

(ቅዱስ ያሬድ፣ ድጓ ዘቃና ዘገሊላ)







### በውስጥ ገጾች


- ✣ በዓለ ጥምቀትን ሁሉም አካል ሊጠብቀው አማኞችም ከምሥጢሩ ሊሳተፉ ይገባል።
- ✣ ወኵሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ
- ✣ ወአግዐዛ እምእኩይ ውስተ ሠናይ
- ✣ የጮቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም
- ✣ በባሕረ ጥምቀት፣ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችና ሌሎች ወቅታዊ ፈተናዎቻቸው


ጥር ፳፻፲፫ ዓ.ም.

# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

ጥር ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት



## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
በዓለ ጥምቀትን ሁሉም አካል ሊጠብቀው አማኞችም ከምሥጢሩ ሊሳተፉ ይገባል።
፫

ዐውደ ስብከት
ወአግዐዛ እምእኲይ ውስተ ሠናይ
፭

ትምህርተ ሃይማኖት
ወኲሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ
፱

ዐቢይ ጉዳይ
የቤተ ክርስቲያን የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችና ሌሎች ይዞታዎቿ ወቅታዊ ፈተናዎች
፲፫

እናስተዋውቃችሁ
የጮቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም
፲፱

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
፳፩

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
ኢየሱስ ወደ ሰርግ ቤት ተጠራ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሄደ።
፳፫

ኪነ ጥበብ
ታሪኩ
፳፱

የነገዋ ቤተ ክርስቲያን
"ሰላም እንዲሰፍን የቤተክርስቲያን ድርሻ"
፴፫


"ማኅበረ ቅዱሳን" እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩፩-፫-፩፪-፪፫-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፫፲፲፯፫
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፫-፩፯-፱፩

ም/ዋና አዘጋጆች
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፯፪፲

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ዲ/ን ኅሊና በለጠ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ሌይ አውት ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሓፊ
ገነት ታደሰ

# በዓለ ጥምቀትን ሁሉም አካል ሊጠብቀው አማኞችም ከምሥጢሩ ሊሳተፉ ይገባል።

## የማኅበሩ መልእክት

የጌታችን ዐበይት በዓላት የቤተ ክርስቲያናችን ዐበይት በዓላት ናቸው፡፡ ሌሎች የቅዱሳን ጻድቃንና የቅዱሳን መላእክት በዓላት ትርጉም ኖሯቸው ሊከበሩ የቻሉት በጌታችን በዓላት የሚታሰቡ ምሥጢራት በመኖራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የቅዱሳን በዓለ ልደት እንደ በዓል የሚከበረው ጌታችን በልደቱ ልደተ ሰብእን በመቀደሱ ነው፡፡ ሰማዕታት የተሠዉበት ቀንም ልዩ ተደርጎ የሚከበረው ጌታችን በሞቱ ሞታቸውን ስለ ቀደሰው ነው፡፡ እርሱ ተወልዶ ልደታችንን ባይቀድስልን የቅዱሳን ልደት የሚያስደስት፣ ሞቶም ሞታችን ዕረፍት እንዲሆን ባይባርክልን የሰማዕታት መሠዋትም ከንቱ በሆነ ነበር፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን የጌታ በዓላት በልዩ ትኩረትና ድምቀት ይከበራሉ፡፡

ከጌታችን ዐበይት በዓላት መካከል ደግሞ ልደቱ፣ ጥምቀቱ፣ ስቅለቱና ትንሣኤው፣ ዕርገቱ፣ ዳግም ምጽአቱ፣ ወዘተ. በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት ከሌሎችም ይልቅ እጅግ ደምቀው የሚከበሩ በዓላት ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል በዓለ ጥምቀት ታቦተ ሕጉ ከመንበሩ ወጥቶ በተለየ ሁኔታ በዐደባባይ የሚከበር በዓል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የበዓሉ ባሕርይ ከሌሎች በዓላት ይልቅ ብዙ የኅብረተሰብ አካላት የበረከቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጋብዝና፡ ብዙዎችን በአከባበሩ ለማካተትም የተመቸ ነው፡፡ ከቤታቸው ተቀምጠው መንቀሳቀስ የማይችሉ ዐቅመ ደካሞችና አረጋውያን፣ በተለያዩ አደጋዎችና ሕመሞች ጤናቸው ታውኮ በየጓዳውና በየጤና ተቋማቱ የተኙ ታካሚዎች፣ በየጎዳናው ወድቀው የሚያነሣቸውን ያጡ ምንዱባን፣ በሕይወተ ሥጋ ለመቆየት በተሰማሩበት ክፉ ሥራ የተነሣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀርበው ለመሳተፍ ሥነ ልቡናቸው ተቃውሶ በሩቅ ያሉ ምስኪኖች፣ በዓለም ሩጫ ተይዘው ቤተ ክርስቲያንን ለዘነጉ ብኩን ክርስቲያኖች፣ በአሠሪዎቻቸው ጫና ቤተ ክርስቲያንን መሳለም ብርቅ የሆነባቸውና ቤት ተዘግቶባቸው ያሉ የቤት ሠራተኞች፣ ከሃይማኖት መንገድ ወጥተው የሳቱ የጠፉ ልጆች፣ በተለያየ ምክንያት ከመቅደሱና ከታቦቱ ርቀው የተለዩ ሰዎች ሁሉ በረከተ ቤተ ክርቲያንን በቅርበት የሚያገኙበት ተናፋቂ በዓል ነው፡፡

ከእነዚህ መካከል ለአንዳንዶቹ የመጥሪያ ደወልም ነው፡፡ ታቦተ ሕጉ በየበሩና በየሠፈሩ ዞሮ መባረኩ ‹‹ልጄ ሆይ አንተ በተለያየ ሰበብ ብትርቅና ብትረሳኝም፡ እኔ ግን አስብሃለሁና ወደ ቤትህ ተመለስ›› የሚል የአምላክ የፍቅር ድምፅ ያለበት የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ነው፡፡ ልባቸው በመቅደሱ ሆኖ አካላቸው በመድከሙና በመታመሙ በአካል ብቻ ለራቁትም ‹‹ልጄ ሆይ ምንም እንኳን በአካል ብትርቀኝም በመንፈስህ ከእኔ ጋር እንደ ሆንህ አውቃለሁ፤ አንተ ወደ

እኔ ልትመጣ ወድደህና ፈቅደህ ሳለ መድከምና መታመም አግኝቶህ ወይም ሰው በማጣት በአካል ባለመምጣትህ አትዘን፤ እኔ ወደ አንተ እመጣለሁና፤ አንተም ዘወትር ከእኔ ጋር ነህና›› የሚል የጌታችንን አስደናቂ የማጽናኛ ቃልን ያዘለ ተልእኮም ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው ማገልገላቸው ምሥጢሩና ትርጓሜው ረቂቅ መሆኑን ሊገነዘቡትና ሊጠነቀቁለት ይገባል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ብዙ ወጣቶች የበዓሉ አካላት መሆናቸው ከላይ የገለጽነው የበዓሉ አሳታፊነት ውጤት ነው፡፡ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች መመሥረት ወዲህ በሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ዝማሬ መታጀብ የጀመረው የበዓሉ ሒደት፣ ከግቢ ጉባኤያት ምሥረታ በኋላም ብዙ የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ተማሪዎችን በዝማሬ እንዲያገለግሉ ዕድሉን መክፈቱ የታወቀ ነው፡፡ በሰንበት ትምህርት ቤትና በግቢ ጉባኤያት ያልታቀፉ የየአካባቢው ወጣቶች ደግሞ አካባቢን በማጽዳት፣ ለታቦተ ሕጉ ማለፊያ ምንጣፍ በማንጠፍ፣ የጉዞ ሥርዓትን በማስከበር፣ መድረኮችን በመገንባትና በመሳሰሉት የየድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡

በዓሉ የሚያመጣውን ይህን ሁሉ አንድነትና ኅብረት ግን ከበዓሉ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ስትጠቀምበት አይስተዋልም፡፡ ይህ ሁሉ የሰው ኃይል በአስደናቂ ጥምረት በካህናትና በቤተ ክርስቲያን መምህራን እየተመራ በዓሉን በአንድነት ካከበረ በኋላ መበተኑ እጅግ ሊያሳስብ የሚገባ ነው፡፡ ቢያንስ የጥምቀት ማክበሪያ ቦታዎችን ዓመቱን ሙሉ ስለ መጠቀም በአንድነት ሊነጋገርና መርሐ ግብር በማውጣትም በተግባሩ ሊተባበር ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈም ቤተ ክርስቲያን እየተቃጠለችና ምእመናን እየተሠዉና እየተሰደዱ፣ ቤት ንብረታቸውም እየወደመ ባለበት ወቅት ይህ ግዙፍ የሰው ኃይል የመጨረሻ ዓላማው በዓለ ጥምቀትን ማክበር ብቻ መሆን የለበትም፡፡

የቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤያት ይህንን በአጽንዖት ሊያቀዱበት ይገባል፡፡ ወጣቶችን ሰብስበው የማስተማር ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው የየአድባራቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም ይህንን ጉዳይ ከማንም በላይ ሊጨነቁበት ይገባል፡፡ በየአካባቢው የሚገኙ የጽዋ ማኅበራት ከእስከዛሬው በላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር ሊመክሩበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም፡ በዓለ ጥምቀት ከመንፈሳዊ ትርጓሜው በዘለለ፡ የቤተ ክርስቲያንንም ሆነ የሀገርን ገጽታ የሚገነባ ልዩ ዕሴት፤ ከሀገርም በዘለለ የዓለምም ቅርስ እንደ መሆኑ የአማኙ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሀብት መሆኑን በማሰብ የሚመለከተው ሁሉ በዓሉንና የበዓሉን ዕሴቶች በመጠበቅ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል እንላለን፡፡

*የረድኤትና የበረከት በዓል ያድርግልን!*

✞ ✞ ✞

# ወአግዐዛ እምእኲይ ውስተ ሠናይ

## (ቅዱስ ያሬድ፣ ድጓ ዘአስተርእዮ)



ዲ/ን ዐብይ ሙሉቀን

ይህ ዓለም ድካም፣ ውጣ ውረድ፣ ጊዜያዊ ሀብት፣ ወዘተ የበዛበት ኃላፊ ዓለም ነው፡፡ ይህ ዓለም ምንም ኃላፊ፣ ጠፊ ቢሆንም የማይታየውንና የማያልፈውን ሰማያዊውን ዓለም ተስፋ አድርገን ወደ ዘለዓለማዊው ሕይወት የሚያስገባን ሥራ እየሠራን የምንኖርበት ዓለም ነው፡፡ ይህ ዓለም ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ "ዓለሙ ያልፋል፤ ምኞቱም ያልፋል" (፩ዮሐ. ፪፥፲፯) በማለት እንደገለጸልን የሚያልፍ የሚጠፋ እንጂ ለዘለዓለም የምንኖርበት ቦታ አይደለም፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የእመቤታችንን ዕረፍት በአዘከረበት ድጓው "ለዛቲ ብእሲት ሠረቀ ላዕሌሃ ብዕለ ጸጋሁ ለአብ፤ ወአግዐዛ እምእኲይ ውስተ ሠናይ እሞት ውስተ ሕይወት፤ ወረሰየ ይዝክሩ ስማ ውስተ ኵሉ ምድር፤ ለዚች ሴት የአብ ብዕለ ጸጋው በእርሷ ላይ ወጣ፤ ከክፉ ወደ መልካም፣ ከሞት ወደ ሕይወት ነጻ አወጣት ወይም ወሰዳት፤ በምድር ሁሉ ስሟን ይጠሩ ዘንድም አደረገ " በማለት አስረዳን፡፡ በዚህ ምንባብ ሊቁ ሊነግረን የፈለገው በእናታችን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የአብ ጸጋው እንዳደረባት፣ ከክፉ ወደ መልካም፣ ከሞት ወደ ሕይወት እንዳሸጋገራት፣ እንዲሁም በምድር ሁሉ ሰዎች ስሟን ሲዘክሩ እንደሚኖሩ ነው፡፡ ዘርዘር ያለውን ጉዳይ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

## ፩. ብዕለ ጸጋሁ ለአብ

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል "ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" (ሉቃ. 1፥28) በማለት እንዳመሰገናት ሊቁ ቅዱስ ያሬድም ይህ ጸጋ ከባሕርይ አምላክ ከእግዚአብሔር የተገኘ መሆኑን በመግለጽ የአብ ጸጋ ለዚች ሴት ወጣ እያለ ያስረዳል፡፡ የእመቤታችንን ጸጋ ዘርዝሮ ይህን ያህላል ማለት አይቻልም፡፡ መልአኩም "ጸጋን የተመላሽ" አላት እንጂ ጸጋሽ ይህ ነው ብሎ ዘርዝሮ አልተናገረም፡፡ ትውልድም እንዲሁ ጸጋን የተመላሽ እያለ ሲያመሰግናት ይኖራል እንጂ ዘርዝሮ መጨረስ አይችልም፡፡

ሌሎች ቅዱሳን ጸጋ ቢኖራቸውም እንደ እመቤታችን ጸጋን የተመላችሁ አልተባለላቸውም፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በላከው መልእክቱ "መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ስጦታው ልዩ ልዩ ነው፡፡ ጌታም አንድ ሲሆን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች አሉ፡፡" (፩ቆሮ. ፲፪፥፬-፭) በማለት እንደተናገረው ለሰው ሁሉ ሰጪው አንድ ቢሆንም ልዩ ልዩ ጸጋ አለ፡፡ ይሁን እንጂ ሌሎች ፍጥረታት ጸጋን የተመላችሁ አልተባሉም፡፡ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን "ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" ተብላለች፡፡

እንደ ሊቁ አገላለጽ ይህ ጸጋ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ከላይም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው ጸጋው ልዩ ልዩ ቢሆንም ሰጪው አንድ ነው፡፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ በድንግል ማርያም ላይ ወጣ (ታየ) ተባለ፡፡ ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ንጽሕናዋን ጠብቃ እንድትኖር ስላስቻላት የእርሱን ጸጋ መቀበል ብቻ ሳይሆን በተአምረ ማርያም እንደተገለጸው "መልኳ እንደ አምላክ መልክ ነው" ተባለላት፡፡

## ፪. ወአግዐዛ

ነጻነት በባርነት ለተያዘ ሰው ብቻ አይደለም፡፡ አስቀድሞ እንዳይያዝ ማድረግም ነጻነትን ማደል ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የዚህ ዓለም ሐሳብ፣ የሀብት ፍላጎት፣ የሥጋ ምኞት፤ የዐይን አምሮት ያልነበረባት

ንጽሕት፣ ድንግልና ቅድስት ናት። ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም በኖረችበት ዘመኗ ብዙ መከራ ተቀብላለች። ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም በተገለጠ ጊዜ፣ በእርሱ ምክንያት ብዙ መከራ ተቀብላለች፤ ተሰዳለች፤ ተርባለች፤ ተጠምታለች።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ያገኘችው ነጻነት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ምእመናን በላከው መልእክቱ "ክርስቶስ ነጻ አውጥቶናልና። እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትትኑ" (ገላ. ፬፥፴፩- ፭፥፩) በማለት እንደተናገረው ያለ ነጻነት አይደለም። ጥንቱኑ የአዳም ልጅ በሙሉ በተያዘበት የባርነት ቀንበር አልተያዘችምና። ነገር ግን ከላይም እንደተገለጸው ይህ ዓለም መከራ የበዛበት፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሥጋ ሥራ "ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ ጣዖት ማምለክ፣ ሥራይ ማድረግ፣ መጣላት፣ ኵራት፣ የምንዝር ጌጥ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ጥርጥር፣ ፉክክር፣ ምቀኝነት፣ መጋደል፣ ስካር፣ ይህንም የመሰለው ሁሉ ነው" ብሎ በመዘርዘር እንደገለጸልን ይህ ሁሉ የሚሠራበት ነው። በዕረፍቷ ይህ ሁሉ የኃጢአት ሥራ ካለበት፣ መከራ ከበዛበት ዓለም ነጻ ሁናለች። ከዚህ ምንባብ ፅንሰ ሐሳብ ሳንወጣ በአጭሩ ሊቁ ከምን ከምን ነጻ አደረጋት አለን? የሚለውን እንመልከት።

## ሀ. እምእኩይ ውስተ ሠናይ

ሊቁ ነጻ አደረጋት ብሎ ከዘረዘራቸው ነጥቦች አንዱ "ከክፉት ወደ መልካም" ነው። ከላይ እንደተገለጸው ከመልካም ነገር ውጭ በሕይወቷ ሌላ ክፉ ነገር የለም። እርሷ "በሐሳብሽም ንጽሕት ነሽ" የተባለች ስለሆነች ክፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ማሰብም የለባትም። ይሁን እንጂ የኖረችው ክፉ በሚሠራበት ዓለም ነውና ክፉ ሥራ ከሚሠራበት ዓለም መልካም ነገር ብቻ ወደሚታሰብበት፣ ወደሚነገርበትና ወደሚሠራበት ዓለም ወሰዳት እያለ ይነግረናል።

እግዚአብሔር አምላካችን እናቱን ድንግል ማርያምን ከሁሉም ነገር የጠበቃት ገና ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ነው። ይህንም ሐሳብ ቅዱስ ያሬድ "መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ፤ መንፈስ ቅዱስ ከእናቷ ማኅፀ ጀምሮ ጠበቃት" በማለት ያስረዳናል። ገና ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ጠበቃት ያለን ሊቁ አሁን በዚህኛው ክፍል ደግሞ ዕረፍቷን ምክንያት አድርጎ ከክፉ ወደ መልካም ነጻ አደረጋት ሲለን ከላይም እንደገለጽነው ክፉ ከሚሠራበት ዓለም፣ ክፉ ከሞላበት ዓለም መልካም ነገር ብቻ ወደሚታሰብበት ዓለም ወሰዳት ማለቱ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

## ለ. እሞት ውስተ ሕይወት

ሞት በብዙ መንገድ ይተረጎማል። የሥጋ ከነፍስ መለየት፣ ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር መለየት፣ በነፍስ ወደ ሲኦል ብሎም ወደ ገሃነም መውረድ ይህ ሁሉ ሞት ይባላል። የነፍስ ከሥጋ መለየት ጊዜው ይዘገይ ይሆናል እንጂ ለሁሉም ሰው አይቀርም። ማለትም የአንደኛው ይረዝም የሌላኛው ደግሞ ያጥር እንደሆነ እንጂ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ የተሠራ ነው። ይህን አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓው "ኢትፍርህዎ ለሞት ፍርህዋ ለኃጢአት እስመ ሞትሰ ኢየኃድገክሙ ዘበላዕሉ ኀልዩ ወአኮ ዘበምድር፤ ሞትን አትፍሩት ኃጢአትን ፍሯት፤ ሞትማ አይተዋችሁምና የሰማያዊውን አስቡ የምድራዊውንም አይደለም" (ጾመ ድጓ ዘቅድስት) በማለት ይህ የነፍስ ከሥጋ መለየት በሁሉም ዘንድ ያለ እንደሆነ ያስረዳናል።

የነፍስ ከሥጋ መለየት የማይቀር ብቻ አይደለም በሃይማኖት ጸንቶ በጎ ምግባር ሠርቶ ለኖረ ሰው ሕይወቱ ነው። ይህንንም አስመልክቶ ቅዱስ ያሬድ በድጓው " ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይቶሙ ውእቱ እስመ ለጻድቅ ይትሌዓል ቀርኑ በክብር፣ ጻድቃን እለ አሥመርዎ ለእግዚኦሙ ምድረ ብርሀተ ወጽዕዱተ ይወርሱ፤ የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው። የጻድቅ ክብሩ ከፍ ከፍ ይላልና። እግዚአብሔርን ያስደሰቱት ጻድቃን

ብርሀት የሆነች ምድርን ይወርሳሉ።” (ቅዱስ ያሬድ ድጓ) በማለት አስረድቷል። በአንጻሩ ደግሞ በሃይማኖት ሳይኖሩ በጎ ምግባር ሳይሠሩ ለኖሩት ደግሞ የሞት ሞት ነው።

ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር መለየትና በነፍስ ወደ ሲኦል ብሎም ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ ግን ለማንም የተፈቀደ አይደለም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም ሃይማኖቱን አጽንቶ በጎ ምግባር ሠርቶ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገባ ነው። ይሁን እንጂ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንገባም ይፈቅድልናል እንጂ አስገድዶ አያስገባንምና ሰማያዊውን ርስት የሚያስወርስ ሥራ ካልሠራን ልንገባ አንችልም። ስለዚህ በሃይማኖት ጸንቶ በጎ ምግባር ሲሠራ የኖረ ሰው ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባል። በአጭሩ ሞት ማለት የነፍስ ከሥጋ መለየት፣ ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር መለየትና በነፍስ ወደ ሲኦል ብሎም ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ ነው።

እግዚአብሔር ድንግል ማርያምን ከየትኛው ሞት ነው ነጻ ያደረጋት ብለን ስንጠይቅ ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል የነፍስ ከሥጋ መለየት ከላይም እንደገለጽነው በሁሉም የተሠራ ስለሆነ ከዚህ ነጻ አልሆነችም። በመሆኑም ይህን ሞት ቀምሳለች። ሊቁ ይህን ሞት መቅመሷን ብቻ ሳይሆን ሰው ናትና ከሞት ጋር የነበራትን ግንኙነትም ሲገልጽ “እፎኑመ እመ አምላክ በከየት ደንጊፃ ከመ ኵሉ ሰብእ ሞት ሶበ ሐወጸ፣ ዮሐንስ በልብሱ ከደነ ገጻ፤ የአምላክ እናት እንዴት ደንግጣ አለቀሰች? እንደ ሰው ሁሉ ሞት በጎበኛት ጊዜ፤ ዮሐንስ በልብሱ ፊቷን ሸፈናት” (ድጓ ዘአስተርእዮ) በማለት ያስረዳል። አምላክን የወለደች ድንግል ማርያም ሞት ሲመጣባት አይታ ደነገጠች።

ልጇም ይህን ሞት እንድትቀምሰው አድርጓታል። ይህ ያስደነቀው ሊቅ “ለምንት ይዜኃር ኃያል በኀይሉ፤ ወባዕል በብዝኃ ብዕሉ፤ ኢያድለወ ሞተ ክርስቶስ ለሥጋ አባሉ፤ ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለማርያም የዐጽብ ለኵሉ፤ ኃይለኛ በኃይሉ ለምን ይመካል? ባለጸጋስ በሀብቱ ብዛት ለምን ይመካል? ክርስቶስ ሞትን ለሥጋ ዘመዱ (ለእናቱ) አላዳላም። ለሚሞት ሰውማ ሞት ይገባል የማርያም ሞት ግን ለሁሉም ይደንቃል።” (ነግሥ ዘአስተርእዮ) በማለት እጅግ ያስደነቀውን ነገር በማንሣት እኛንም ያስደንቀናል። ስለዚህ ሞትን ለእናቱም አላዳላም ከተባለ ከየትኛው ሞት ነው ነፃ አደረጋት የሚለን? የሚለውን ማንሣትና ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።

ድንግል ማርያም ከሞተ ሥጋ አልቀረችም። ሌሎቹ ሁለቱ ግን ማለትም ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር መለየትና በነፍስ ወደ ሲኦል ብሎም ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ በእርሷ ዘንድ የሌሉ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ካለማየት ነጻ አደረጋት፤ ከኃጢአት ነጻ አደረጋት፤ በነፍስ ወደ ገሃነመ እሳት ከመውረድም ነጻ አደረጋት። ይህ ብቻ አይደለም ኃጢአት ከሚሠራበት ዓለምም ነጻ አደረጋት። ሞት ካለበት ማለት ኃጢአት ከሚሠራበት፣ የሥጋ ምኞት ከነገሠበት፣ ኃላፊ ጠፊ የሆነው ሁሉ ካለበት ዓለም ነጻ አወጣት። ከዚህ ሁሉ ዓለም ነጻ አውጥቶ ሕይወት ወዳለበት፣ ዘለዓለማዊ ዕረፍት ወዳለበት ደስታው ወደማያልቅበት ዓለም ወሰዳት ማለት ነው።

## ፫. ይዝክሩ ስማ ውስተ ኵሉ ምድር

እግዚአብሔር አምላካችን በነቢዩ በኢሳይያስ ላይ አድሮ “ሰንበቴን ቢጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ቢመርጡ በቃል ኪዳኔም ጸንተው ቢኖሩ በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ ስም የሚያስጠራ ቦታን እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋ የዘለዓለም ስምንም እሰጣቸዋለሁ” (ኢሳ.፶፮፥፬-፭) በማለት ለወዳጆቹ ሊሰጣቸው የሚችለውን ጸጋ ተናግሯል። ከላይ የተዘረዘሩትን ብቻ ሳይሆን የአምላክ እናት

የሆነች ድንግል ማርያምን ዙፋኑ ያደረጋት እናቱን ደግሞ ከዚህ በላይ የሆኑ ጸጋዎችን አድሏታል። ስለዚህ በምድር ሁሉ ስሟን እንዲጠሩ አደረገ በማለት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ያስረዳናል።

ይህን ሐሳብ በመልአኩና በቅድስት ኤልሳቤጥ አንደበት ከተመሰገነችና ጌታን ከፀነሰች በኋላ ከዚህ በኋላስ በአንድ መልአክና በአንዲት ሴት ብቻ ተመስግኜ አልቀርም "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" (ሉቃ.፩፥፵፰) ስትል አስቀድማ ተናግራለች። በእርሷ አንደበት "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ብላ እንደተናገረች፣ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ "ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ" (መዝ.፵፬፥፲፯) በማለት እንደተናገረ ሌሎችም ነቢያት አስቀድመው በትንቢት እንደተናገሩላት እግዚአብሔርም ይህን ጽኑዕ ቃል ኪዳን አጽንቶላት በምድር ሁሉ ስሟን እንዲጠሩ አደረገ።

> **"ኵሉ ትውልድ ያስተበፅዑኪ፤ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል"**

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ "ኵሉ ትውልድ ያስተበፅዑኪ፤ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል" (ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ) በማለት ተናግሯል። እግዚአብሔር አምላካችን ከዚህ ውጣ ውረድ ካለበት፣ ድካም ከበዛበት፣ ኃጢአት ከሚሠራበት፣ ፈቃደ ሥጋ ከነገሠበት ዓለም ወስዶ በቀኙ እንድትቀመጥ አደረገ። ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት "ወትቀውም ንግሥት በየማንከ፣ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኍብርት፤ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች" (መዝ.፵፬፥፱) በማለት እንደተናገረ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠች።

ከሞት ወደ ሕይወት አሸጋገራት ማለት ከላይም እንደተገለጸው ሞት ነበረባት ማለት አይደለም። ሞት በሰፈነበት ዓለም ስትኖር ሞት ያልነካት፣ ሞት ሰልጥኖ በነበረበት ዘመን ንጽሕት ሁና የተገኘች ከፍጥረታት ሁሉ የተለየች ናት። ምንም የተለየች ብትሆንም ሞት ባለበት ዓለም ኖራለችና ከዚህ ሞት ካለበት ዓለም ሞት ወደሌለበት ሕይወት ወደ ሰፈነበት ዓለም ወሰዳት በማለት ያስረዳል።

ከዚህ ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ወስዶ ትውልድ ሁሉ ለዘለዓለም ሲዘክሯት፣ በስሟ ሲማጸኑ፣ ለምነው የፈለጉትን ሲያገኙ እንዲኖሩ አደረገ። ለምን ያመሰግኗታል የሚል ቢኖር ደግሞ ይህን አስመልክቶ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ "ሰብእ ወእንስሳ ወኵሉ ዘሥጋ ያስተበፅዑኪ እስመ ለዘይሴስዮሙ በሐሊበ አጥባትኪ ሐፀንኪዮ፤ ሰው እንስሳና ሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑሻል። የሚመግባቸውን በጡትሽ ወተት አሳድገሽዋልና" (አርጋኖን ዘሰኑይ) በማለት ቅድስት ድንግል ማርያምን ፍጥረታት ሁሉ እንደሚያመሰግኗት ከገለጸ በኋላ ለምን እንደሚያመሰግኗት ምክንያቱን ሲያብራራ ደግሞ ፍጥረታትን ሁሉ የሚመግበውን አምላክ ጡቷን አጥብታ በማሳደጓ እንደሆነ ያስረዳል።

በአጠቃላይ እግዚአብሔር አምላካችን እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ዕረፍተ ሥጋን አድሎ ክፉ ሥራ ከሚሠራበት ዓለም መልካም ሥራ ወደሚሠራበት ዓለም፣ ኃጢአት፣ እልቂት ሞት፣ ወዘተ ካለበት ዓለም ሕይወት ወዳለበት ዓለም ወሰዳት። እርሷን ከዚህ ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ቢወስዳትም ዘለዓለማዊና የማይጠፋ ስም አድሏታልና ትውልድ ሁሉ ስሟን ሲዘክሯት እንዲኖሩ አደረገ። እኛንም ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም በረከት አድሎን፣ በሃይማኖት ጸንተን በንጽሕና በቅድስና ኑረን ነጻነት ወደ ሰፈነበት ዓለም እንዲያሸጋግረን እግዚአብሔር ይፍቀድልን አሜን።

✞ ✞ ✞

# ወኵሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ

(ቅዱስ ኤፍሬም)

## ትምህርተ ሃይማኖት

በዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እመቤታችንን ባመሰገነበት በዕለተ ሰኑይ ውዳሴ ማርያም ላይ በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ፍጥረታት በሙሉ ደስ እንዳላቸው ይናገራል፡፡ እንደሚታወቀው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ሳይለይ በተለየ አካሉ ከሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ደንግል ማርያም ሥጋና ነፍስ ነሥቶ ፍጹም ሰው የሆነው የሰው ልጆችን ለማዳን ነው፡፡ በዚህ ደስ ሊለን የሚገባን እኛ የሰው ልጆች ነን፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ግን ፍጥረት ሁሉ ደስ አለው ብሎናል፡፡ ለመሆኑ ፍጥረታት የተባሉት እነ ማን ናቸው፤ ለምን ደስ አላቸው ብለን ስንጠይቅ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፍጥረታት የተባሉት መላእክት፣ እንስሳትና አራዊት፣እንዲሁም ደቂቀ አዳም ናቸው፡፡ ብለው በሦስት ከፍለው አስቀምጠውልናል፡፡

## ሀ. መላእክት፡-

መላእክት የሚለው ስም ግብራቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ ቃሉ የግእዝ ሲሆን በግሪክ አንጌሎስ (Angelos)፣ በዕብራይስጡ ደግሞ መለክ፣ “Mal’ak” ከሚሉት ቃላት የአቻነት ትርጉም ያለው ነው፡፡ የተላከ (messenger) የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ በግእዙም መላእክት የሚለው ቃል፡- ለአከ፣ ተልእከ፣ ላከ፣ ተላከ ልኡክ ከሚሉ ግሶች የሚገኝ ሲሆን መላላክን፣ ማገልገልን፣ መልእክተኛ መሆንን ያመለክታል፡፡ (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፫፻፶፬)

መጽሐፍ ቅዱስም መልአክ የሚለው ቃል ተላኪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ “ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ፡ ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ” ተብሎ የተጻፈው ሐሳብ ይህን ትርጉም የሚያመለክት ነው፡፡ (የሐዋ.፲፪፥፲፩) በትንቢተ ዳንኤልም ላይ “አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ” የሚል ኀይለ ቃል እናገኛለን፡፡ (ዳን.፮፥፳፪) በእነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች “መልአኩን ልኮ” በሚለው ሐረግ መልአክ የሚለው ቃል የሚላክ፣ መልእክተኛ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡

ከቃሉ ትርጉም ተነሥተን መላእክት የሰው ልጅን ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ ለማዳን፣ ይልቁንም በምድር በሚገጥመው ፈተና ተስፋ ሳይቆርጥ በሃይማኖት ጸንቶ በምግባር ቀንቶ፣ በሕይወቱ ፈጣሪውን አስደስቶ ሰማያዊውን መንግሥት ለመውረስ እንዲበቃ ለማገዝ የሚላኩ ፍጥረታት ናቸው፡፡ ሐዋርያው ይህን እውነት ሲናገር ነው “ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?” ሲል የጻፈልን፡፡ (ዕብ.፩፥፲፬)

ልበ አምላክ የተባለ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል” (መዝ.፴፫፥፯) እንዳለን ዘወትር ወደ ሰው ልጅ ይላካሉ፡፡ በመከራ የወደቁትንም እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያደርግላቸው ይማጸናሉ፡፡

ቅዱሳን መላእክት እንኳን በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ለተፈረደበት ለአዳም በኃጢአታቸው ምክንያት ሰባ ዘመን በአሕዛብ ነገሥታት እንዲቀጡ ለተፈረደባቸው ሕዝበ እስራኤልም “አቤቱ፥ የሠራዊት ጌታ ሆይ፥ እነዚህ ሰባ ዓመት የተቈጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው?” በማለት በምልጃ ደጅ ይጠኑ እንደነበር ተጽፎልናል፡፡ (ዘካ.፩፥፲፪) እግዚአብሔርም ባለሟሎቹ ናቸውና ልመናቸውን ሰምቶ ቸል አላለም፤ ጸሎታቸውን ሰምቶ ተስፋ ሰጥቶ አስደሰታቸው እንጂ “እግዚአብሔርም ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው” እንዲል፡፡ (ዘካ.፩፥፲፫) ጌታችን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቅዱሳን መላእክት ከሰው ልጆች ጋር ያላቸውን ፍቅር ሲናገር “ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ሁልጊዜ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁ” ብሏል። (ማቴ.፲፰፥፲)

እንግዲህ ቅዱስ ኤፍሬም ስለ ወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ሲናገር “ፍጥረት ሁሉ በመምጣትህ ደስ አለው” ብሎ ከተናገረላቸው ፍጥረታት መካከል አንዱ መሆናቸውን እንገነዘባለን። ይህስ እንደምን ነው ቢሉ መላእክት ከእግዚአብሔር ተልከው ሥጋዌውን ለነቢያት ነግረዋቸው ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት ተናግረዋል። ይህ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞ፣ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ አይተነው “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፤ በሰማያት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን በምድርም ሰላም ለሰውም ልጅ በጎ ፈቃድ ሆነ” ብለን አመስግነነው በክብር ላይ ክብር፣ በጣዕም ላይ ጣዕም በጸጋ ላይ ጸጋ ተጨምሮልን እያሉ ሲመኙ ይኖሩ ነበር። ይህ ተደርጎላቸው ደስ ብሏቸው አመስግነዋልና ደስታቸው ይህ ነው። (የሰኞ ውዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ)

በርግጥ በጌታ መወለድ ቅዱሳን መላእክት ተደስተዋል ወይ የሚለውን ለማወቅ በቤተ ልሔም የሆነውን ማስታወስ በቂ ነው። “ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መጡ። ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ” እንዲል። (ሉቃ.፪፥፲፫-፲፬) ለመሆኑ መላእክት ስለምን ደስ አላቸው ለሚለው ጥያቄ እስካሁን ከተመለከትነው በተጨማሪ የውዳሴ ማርያም አንድታ ትርጓሜ የሚከተለውን ብሏል።

መላእክት ደስ አላቸው ማለቱ ታላቅ ወንድም ለታናሽ ወንድሙ በተደረገለት ደስ እንደሚለው ያለ ደስታ ነው። መላእክትም ለሰው ተድላ ደስታ ሲደረግለት ባዩ ጊዜ ለራሳቸው እንደተደረገላቸው አድርገው ደስ ይላቸዋልና። (ዝኒ ከማሁ) “መላእክት ለሰዎች ስለተደረገው ክብር እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት ተረዳህን ይልቁንም ኃጢአት ስለተሠረየችልህ ለእኛ የተደረገውንም ክብር ለእነርሱ እንደተደረገ አድርገው ያዩታል” እንዲል። (ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ ፷፮፥፴፱)

## ለ.እንስሳትና አራዊት፡-

ፍጥረት ያላቸው እንስሳትና አራዊት ናቸው። ይህ እንደምን ነው ቢሉ በቤተሰብእ ልማድ ነው፤ ቤተሰብ ጌታው ሲሾምለት ሲሸለምለት ደስ እንደሚለው እነሱም ጌታቸው አዳም ከፈጣሪያቸው ጋር ሲጣላ አዝነው ነበርና በጌታ መወለድ ከጌታው ስለታረቀላቸው ደስ ብሏቸዋል። እንዲሁም ለራሳቸው በተደረገላቸው ነገር ደስ ብሏቸዋል። ቀድሞ በኖኅ ዘመን የሰው ልጆች በሠሩት ኃጢአትና በደል ምክንያት እግዚአብሔር ምድሪቱን በውኃ ሲያጠፋት ኃጢአት በደል የሌለባቸው ማለትም አእምሮ ዕውቀት ያልተሰጣቸው ጽድቅና ኩነኔም ለይተው የማያውቁና የሌለባቸው ፍጥረታት በሙሉ ከሰው ልጆች ጋር አብረው ጠፍተው ነበረና ከእንግዲህ ወዲህ ጌታችን አዳም ከፈጣሪው ጋር ከታረቀልን እኛም ሁለተኛ ጥፋት አያገኘንም ሲሉ ደስ ብሏቸዋል። (የሰኞ ውዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ)

ከእንስሳት መካከል አህያ እና ላም በጌታ መወለድ ደስታቸውን በቤተ ልሔም ዋሻ እስትንፋሳቸውን በመገበር ገልጸዋል። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ነቢዩ ኢሳይያስ “በሬ የገዢውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀም፥ ሕዝቤም አላስተዋለም” (ኢሳ.፩፥፫) በማለት ጌታ ሕዝበ እስራኤልን የገሠጸበትን ትንቢት ሲተረጕሙ “ቤት ያለው ጎል (ግርግም) ነው ጌታ በእሷ ተወልዶባታልና አህያና በሬ ጌታ የተወለደበትን አውቀው እስትንፋሳቸውን ገብረውለታል። አይሁድ ግን በቤተ ልሔም ዋሻ በግርግም የተወለደው አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን አላወቁትም ብለዋል። (ትንቢተ ኢሳይያስ አንድምታ ትርጓሜ)

## ሐ. ደቂቀ አዳም

ሌላኛው ፍጥረት ተብሎ የተነገረው አዳምና ልጆቹ ናቸው። ከፍ ብለን ያየናቸው እንስሳትና አራዊት “ለኃጥአን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል” እንዲባል የሰው ልጅ ከፈጣሪው

ጋር በመጣላቱ ምክንያት ሲመጣባቸው ካለው መዓት በመዳናቸው ምክንያት ደስታቸውን ገልጸዋል፡፡ በወልደ እግዚአብሔር ከሰማያት መውረድና መወለድ ትልቅ ደስታ የተደረገልን ግን እኛ የሰው ልጆች ነን፡፡ ጌታም የነሣው የመላእክትና የሌሎች ፍጥረታትን ሥጋ አይደለም፤ የሰውን ነው እንጂ፡፡ (ዕብ.፪፥፲፮) ለምን ቢሉ የበደለው፣ የወደቀው፣ ሞት የተፈረደበት፣ አዳም ነውና፡፡

ስለዚህ የወደቀውን ለማንሣት፣ የተፈረደበትን ነፃ ለማውጣት፣ የሞተውንም ሕያው ለማድረግ ያንኑ የአዳምን ሥጋ ተዋሕዷል፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ምሥጢረ ተዋሕዶን ሲናገር "የቃል ገንዘቡ ለሥጋ ገንዘቡ ሆነለት፣ የሥጋም ገንዘቡ ለቃል ገንዘብ ሆነለት" (ድርሳነ ቄርሎስ ፸፰፥፫) እንዳለው እግዚአብሔር ወልድ የሰው ልጅን ሥጋና ነፍስ ነሥቶ በተዋሐደ ጊዜ ባሕርያችን ሕያውነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነውን መለኮታዊ ባሕርይን ገንዘቡ አድርጓል፡፡

**"ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፤ በሰማያት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን በምድርም ሰላም ለሰውም ልጅ በጎ ፈቃድ ሆነ" ብለን አመስግነነው በክብር ላይ ክብር፣ በጣዕም ላይ ጣዕም በጸጋ ላይ ጸጋ ተጨምሮልን እያሉ ሲመኙ ይኖሩ ነበር፡፡**

እንግዲህ የታመመውን የሰው ልጅ ለማዳን ከበሽተኛው አዳም የተሻለ ያልታመመ ሐኪም ፣ ወንጀል የሌለበት ዋስ ጠበቃ፣ ነቀዝ ያላበላሸው ንጹሕ የመሥዋዕት ስንዴና ፍጹም ካህን ያስፈልገን ነበረና የሕይወት መገኛ፣ የባሕርይ ሕይወት፣ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሰው ሆኖልናል፡፡ ስለ እኛም መከራ ተቀበለ ሞተ ተቀበረ፣ የሞትንም ኃይል ሽሮ፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በእርሱ ሞትና ትንሣኤም ድኅነታችን ተፈጸመልን፡፡ ራሱ የመሥዋዕት በግ ራሱ የመሥዋዕቱ አሳራጊ ካህን እሱ ራሱ የመሥዋዕቱ ተቀባይና ይቅር ባይ አምላክ ሆነልን፡፡ ርቀን የነበርነውን አቀረበን፤ "አዳም ሆይ ወዴት ነህ" ብሎ በአዳም አንጻር ሲጠራን ድምፁን እንፈራና እንሸሽ የነበርን፣ በልጅነት ፍቅር የምንጠራ ሆነናል፡፡ "አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና" እንዲል፡፡ (ሮሜ ፰፥፲፭) ከልጅነት በላይ ጸጋ፣ ከአባትነት በላይ ስጦታ ደግሞ ሊኖር አይችልም፡፡

ይህም ሁሉ የሆነልን ወልደ እግዚአብሔር ከሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ሥጋና ነፍስ ነሥቶ ሰው በመሆኑ ነውና "በመምጣትህ ደቂቀ አዳም" ደስ ይላቸዋል አለን፡፡ አዎን ደስ ሊለን ይገባል፡፡ ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከገሃነመ እሳት ወደ መንግሥተ ሰማያት ከባርነት ወደ ልጅነት፣ ከተገዥነት ወደ ወራሽነት የተሻገርንበት ቀን ነውና ደስ ይበለን፡፡ እርሱ ሰው ሲሆን እኛ አማልክት ዘበጸጋ ሆነናልና ደስ ይበለን፤ እርሱ በበረት ሲወለድ እኛ ወደ ንጉሡ ዙፋን ፊት ቀርበናልና ደስ ይበለን፤ እርሱ ወደ ግብፅ ሲሰደድ እኛ ወደ ርስታችን ገነት ተመልሰናልና ደስ ይበለን፣ እርሱ ሲሞት እኛ ሕያዋን ሆነናልና ደስ ይበለን፤ በትንሣኤውም ትንሣኤያችን ተረጋገጠልን፣ የበደላችን ዕዳ በሞቱ ተከፈለልን፤ የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ሰነቅን፤ ታዲያ ከዚህ በላይ የሚያስደስት ምን አለ? ስለዚህ ደስ ሊለን ይገባል፡፡ ነገር ግን ሁለት ነገሮችን ሳንዘነጋ ነው፡፡

፩ኛ ደስታችን ፍጹም እንዲሆን ከእኛ የሚጠበቀውን

ማድረግን፡- እንግዲህ በጌታ ልደትና ጥምቀት፣ ሞትና ትንሣኤ ዕዳችን ተክፍሎልን የዕዳ ደብዳቤያችን ተደምስሶልን ተስፋችን እንደለመለመ ይታወቃል። ይሁንና የእኛ ድርሻ መኖሩን መዘንጋት የለብንም። በየዓመቱ ጌታ ተወለደልን፣ ተጠመቀልን፣ ተሰቀለልን፣ ሞትንም ድል አድርጎ ተነሣልን ወዘተ እያልን በዓላትን ስናከብር፤ እንደ ሉተራውያን በቃ ድኅነታችን ተፈጽሞልናል፤ ከእኛ የሚጠበቀው ይህን ማመን ብቻ ነው እያልን አይደለም። አዎን ድኅነታችን ተፈጽሞልናል እኛ ግን ከተፈጸመልን ድኅነት ተካፋይ ለመሆን ዕለት ዕለት መትጋት ይጠበቅብናል። ይህም ጌታ እንደተወለደልን በጥምቀት ዳግመኛ በመወለድ፤ እንደተጠመቀልን ለሥርየተ ኃጢአት በመጠመቅ፣ ስቅለቱንና ትንሣኤውንም ስናስብ የተቆረሰልንን ሥጋ የፈሰሰልንም ደሙን በመቀበል እና ይህን የመሳሰሉ በጎ ምግባራት በማድረግ ሊሆን ይገባል።

፫ኛ ደስታችን አምላካችንን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መሆን አለበት፡- ጌታ ከኀጢአት ሊያድነን ሲወለድ እኛ ይህን ደስታ ለመግለጽ ወደ ኀጢአት አለመሄዳችን ማስተዋል ይገባናል። ደስታችን የተደረገልንን ውለታ በማሰብ ከሆነ ጌታ ራሱ "እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና" (ዮሐ.፲፫፥፲፭) እንዳለን ለሌሎች መልካም በማድረግ ደስ ይበለን።

> **በጌታችን መወለድ መላእክት፣ እንስሳትና አራዊት እንዲሁም ደቂቀ አዳም ተደስተዋል። ዛሬም በዓሉ ለሁሉም ደስታን ያጎናጽፍ ዘንድ ብቻየን ልብላ፣ ብቻየን ልጠጣ፣ ብቻየን ላጊጥ ወዘተ ሳይሉ ያለው ለሌለው እያበላ፣ እያጠጣና እያለበሰ መከበር አለበት።**

በክርስትና አስተምህሮ ደስታ የሚገኘው ለራሳችን በምናደርገው ብቻ አይደለም። ይልቁንም ለወንድሞቻችን በምናደርግላቸው ነው እንጂ። ብዙ በመብላትና ያለ ልክ በመጠጣት ለብሰን በማጌጥና ይህን በመሰለ ሁሉ አይደለም ደስታችን ሊሆን የሚገባው። እንደጌታችን ትምህርት የተራቡትን በማብላት የተጠሙትን በመጠጣት፣ የታረዙትን በማልበስ ነው እንጂ። ከዚህ በተጨማሪ ዝናብ ያስገኘች ትንሽዋ ደመና፣ ኅብስት ያለባት መሶበ ወርቅ እየተባለች በብዙ ኅብር ከምትመሰለው ከእመቤታችን በቤተ ልሔም ዋሻ የተወለደውን ጌታ ከመላእክቱና ከእረኞቹ ጋር አብረን ማመስገን፣ ከሊቃውንቱ ጋር አብረን መዘመር፣ ይገባናል። ደስታችን ደግሞ ሰማዕያኑ መላእክትንም ደስ የሚያሰኝ ሊሆን ይገባል። እንደሚታወቀው የሰማይ ሠራዊት መላእክት ስለእኛ ደስ የሚላቸው ንስሓ ገብተን ሥጋውንና ደሙን ተቀብለን ለሰማያዊ ርስታችን ስንዘጋጅ ነው። "ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል" እንዲል። (ሉቃ.፲፭፥፯)

በአጠቃላይ በጌታችን መወለድ መላእክት፣ እንስሳትና አራዊት እንዲሁም ደቂቀ አዳም ተደስተዋል። ዛሬም በዓሉ ለሁሉም ደስታን ያጎናጽፍ ዘንድ ብቻየን ልብላ፣ ብቻየን ልጠጣ፣ ብቻየን ላጊጥ ወዘተ ሳይሉ ያለው ለሌለው እያበላ፣ እያጠጣና እያለበሰ መከበር አለበት። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሲሰጠን እኛም ያለንን ልናካፍል የተራቡትን ልናበላ ይገባናል። የተሰጠንን ጸጋ አጽንተን የምንኖረውና ወደከፍተኛዋ ጸጋና ክብር የምንሸጋገረው እርሱ ራሱ ከሰጠን ላይ ከጥቂቷም ቢሆን ለሌላ ስንሰጥ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ሁላችንም በሃይማኖት ጸንተን በጎ ምግባር ሠርተን ንስሓ ገብተን ሥጋውንና ደሙን ተቀብለን የመንግሥቱ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች እንድንሆን እግዚአብሔር ይፍቀድልን አሜን።

✞ ✞ ✞

# የቤተ ክርስቲያን የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችና ሌሎች ይዞታዎቿ ወቅታዊ ፈተናዎች

*ክፍል ሁለት*



*ዲ/ን ጎሊና በለጠ*

## የጥምቀት ማክበሪያ ይዞታዎች የመነጠቃቸውና የመወረራቸው ምክንያት

የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች የመነጠቃቸውና የመወረራቸው ምክንያቶች ብዙና ውስብስብ ቢሆኑም፡ ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው በአጭሩ እንያቸው፡-

፩. ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት እና የመስቀል ማክበሪያ ቦታዎቿን በሕግ አስከብራ ያለመያዝ ቸልተኝነትና ከክብረ በዓል በኋላ ለይዞታዎቹ ትኩረት አለመስጠት፣

ይህ በግልጽ የሚታይ የእኛው ቸልተኝነት ነው። ክፍተቱን በደንብ ለመረዳት በሦስት ከፍለነው እንየው፡-

**ሀ. ይዞታዎቹን አጥሮ አለማስከበርና መዘንጋት** - አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ይዞታዎቹን በዓላቱ ሲደርሱ እንጂ ከዚያ በኋላ የሚያስታውሷቸውም አይመስልም። ቦታዎቹን አጥሮና ከልሎ ማስከበር ሲገባ በዓሉ ሲደርስ ብቻ ባለ ይዞታ እየመሰልን ብዙዎች ወደ ይዞታችን እስኪገቡ ድረስ መዝጊያ እንደሌለው ቤት ቸል አልናቸው።

**ለ. ተጠሪ አካል አለመኖር** - አብዛኞቹን ባሕረ ጥምቀቶች በርካታ አድባራትና ገዳማት በጋራ ይጠቀሙባቸዋል። ነገር ግን ከመካከላቸው ይዞታውን በእኔነት ስሜት ዘወትር የሚከታተል አካል የለም።

**ሐ. በጉዳዩ ላይ ማዕከላዊ አመራር አለመኖር** - ባሕረ ጥምቀቶችንና የመስቀል አደባባዮችን የቤተ ክርስቲያን ይዞታነት በተመለከተ የሚንቀሳቀስና የሚያስከብር በመዋቅር የታወቀ የሥራ ዝርዝር ያለው ማዕከላዊ አካል አለመኖሩም ለተከሰቱት ጉዳዮች አንድ ምክንያት ነው።

፪. *መንግሥት መመሪያ አውጥቶ በመንግሥት ተቋማት ሥር ይዞታዎቹ እንዲተዳደሩ ሲያደርግ ጉዳዩን በቸልታ መመልከት*

፫. በማስተር ፕላን አለማካተት - በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ከማስተር ፕላን ትግበራ በፊት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ፣ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከከተማ መመሥረት እና ከማስተር ፕላን ጥናት በፊት የነበሩ ይዞታዎች፤ ማስተር ፕላኑ፣ የከተማ መመሥረት እና መስፋፋት ታሳቢ ሳያደርጋቸው ወይም ሆን ተብለው ሳይካተቱ ቀርተዋል (አውጥተዋቸዋል)።

፬. በልማት ሰበብ መንጠቅ- የጥምቀት ማክበሪያ ይዞታዎችን በከተማ መስፋፋት ምክንያት የሚገኙበት ቦታን ለሌላ ልማት መውሰድ ወይም መንጠቅ ሌላው ፈተና ነው። ይህ ሲደረግ ደግሞ የሚመለከታቸው አካላት በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያንን ሳያማክሩ ቦታውን ስለሚወስዱት ችግሩን አስከፊ ያደርገዋል።

፭. የአፅራረ - ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ - ኦርቶዶካሳዊት ሃይማኖትን ጠል እና ዕሴቶቿን የማጥፋት ተልእኮ ሌላኛው ምክንያት ነው። በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው በሥልጣንም ሆነ በልማት ስም ቤተ ክርስቲያንን የሚበድሉና ያላትን ሀብት ለመንጠቅ የሚሮጡ ብዙ ናቸው።

፮. የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ሚናቸውን አለመወጣት - ጥምቀትና ደመራን የመሳሰሉ በዓላት የሀገር ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅርስ ከመሆናቸውም ባሻገር ለሀገር ከፍተኛ ገቢን የሚያስገቡ የቱሪስት መስህቦች ሆነው ሳለ ባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ቅርስ ጥበቃ ባለ ሥልጣንን የመሳሰሉት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝም ብለው ማየታቸው እጅግ የሚያስተቻቸው ነው። በገቢ ረገድ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ መንግሥት በከፍተኛ መጠን እየተጠቀመ እነዚህ መሥሪያ ቤቶች ለይዞታዎቹ መከበር ቤተ ክርስቲያንን አግዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባ ነበር።

፯. *የመንግሥት መመሪያዎች ድክመትና የአተረጓጎም ስሕተት*

ከመመሪያና ከአተገባበራቸው ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ

ከተማ አስተዳደር ለሃይማኖት ተቋማትና ለአምልኮ ማካሄጃ ቦታ አፈቃቀድ በ፳፻፬ ዓ.ም. እና ፳፻፲ ዓ.ም. የወጡ መመሪያዎችን እስኪ በጥቂቱ ለማየት እንሞክር፡-

**ጥምቀትና ደመራን የመሳሰሉ በዓላት የሀገር ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅርስ ከመሆናቸውም ባሻገር ለሀገር ከፍተኛ ገቢን የሚያስገቡ የቱሪስት መስህቦች ሆነው ሳለ ባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ቅርስ ጥበቃ ባለ ሥልጣንን የመሳሰሉት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝም ብለው ማየታቸው እጅግ የሚያስተቻቸው ነው።**

## የማምለኪያ ቦታ በአዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በሕጋዊ መንገድ ላገኟቸው ይዞታዎች የማረጋገጫ ካርታ ጥያቄዎችን መዋቅሩን ጠብቀው እስከ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት አቅርበዋል። አሁንም በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። ሆኖም በአብያተ ክርስቲያናቱ የሚነሡ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫን የተመለከቱ ብዙ ቅሬታዎች አሉ። የይዞታ የማረጋገጫ ካርታና በምዝገባ የአምልኮት ቦታ ተጨማሪ ጥያቄዎች በወቅቱ አለመመለሳቸውና የመመሪያ አተረጓጎምና አፈጻጸም ክፍተቶች መኖራቸው ለቅሬታዎቹ ምንጮች ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እስከ ፳፻፬ ዓ.ም. ድረስ በሃይማኖት ተቋማት በተለያየ ጊዜ በልዩ ልዩ መንገድ ለተያዙ ይዞታዎች ማረጋገጫ ካርታ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚያስችል መመሪያም ሆነ የአሠራር ግንኙነቶች አልነበሩትም።

በ፳፻፬ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሃይማኖት ተቋማት የተያዙት ይዞታዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ቁጥር ፪/፳፻፬ ዓ.ም. በማጽደቅ

- ከአዋጅ ፵፯/፷፯ ዓ.ም. በፊት የተያዘ (በምን አዋጅ ነጋሪት ጋዜጣ ወይስ አዲስ ልሳን ይገለጽ)
- ከአዋጅ ፵፯/፷፯ ወዲህ ያለ፣ ግንቦት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. የተያዙ (GIS) ወይም በ፲፱፻፺፯ Linemap የሚታዩ
- ከግንቦት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. እስከ መስከረም ፱/፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በ፲፱፻፺፬ (፲፱፻፺፯) Line map የሚታይ እና ሌሎችም የአሠራርና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ ወደ ተግባር በመግባት በተለያዩ ጊዜያት የሃይማኖት ተቋማት ለሚያነሡአቸው የዓመታት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል። ሆኖም ግን መመሪያው በራሱ ክፍተት ያለበት ነበር።

## የመመሪያው ክፍተት

በ፳፻፬ ዓ.ም. የወጣው መመሪያ ፬/፪/፳፻፬ ዓ.ም. ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላም የነበሩ የይዞታ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ቢደረግም፡ መመሪያው እስከ መስከረም ፱/፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ድረስ ብቻ የተያዙትን ይዞታዎች ሕጋዊ ለማድረግ የፀደቀ በመሆኑ ከ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ወዲህ የተያዙ የሃይማኖት ተቋማት ሕጋዊ የሆኑበት መመሪያ የለም። በመሆኑም የበርካታ ሃይማኖት ተቋማት የአምልኮ ማካሄጃ ቦታ ጥያቄዎች አሁንም ድረስ ምላሽ አልባ ናቸው።

ለ፲፬ ዓመታት ያህል በሕጋዊ መንገድ ያገኙነው (የያዝነው)

የአምልኮ ማካሄጃ ቦታ ሕጋዊ ሰነድ ይሰጠን ጥያቄዎች የአስተዳደር ቢሮውን አጣበውታል። ነገር ግን መልሱ የሚመለስበት መመሪያም የለም። መልስም የለም።

## ያልተፈጸመው ሌላው መመሪያ

የከተማው አስተዳደር በ፲፱፻፺ ዓ.ም. ለሃይማኖት ተቋማት ለአምልኮት ማካሄጃ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር ፩/፲፱፻፺ ግንቦት ፲፱፻፺ ዓ.ም.

- የአምልኮ ማካሄጃ ቦታ በምደባ ስለ መፍቀድ
- ለአምልኮ ማካሄጃ አገልግሎቱ የሚመደብ የቦታ ስፋት
- በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት መካከል የሚኖረው ርቀት
- በአካባቢው ከሚገኙ ከራሱ ነባር የአምልኮ ቦታዎች አዲስ የተጠየቀው የአምልኮ ቦታ ቢያንስ በሁለት አቅጣጫ ፫ ኪሎ ሜትር ራዲየስ ርቀት ሊኖረው እንደሚገባ

በመደንገግ የማምለኪያ ቦታን ለመስጠት የሚያስችል ወጥ መመሪያን አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል።

ነገር ግን ከከተማው የመሬት ሊዝ ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፷ ጋር ተገናዝቦ የሃይማኖት ተቋማት በፍትሐዊነት የአምልኮ ማካሄጃ ቦታ እንዲያገኙ ፀድቆ ሥራ ላይ ቢውልም በመመሪያው መሠረት በምደባ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቦታ ተሰጥቶ አያውቅም። መደምደም ይቻል ይሆን) (በቅርቡ ለቤተ ክርስቲያናችን ሦስት ቦታዎችን ብቻ በልዩ ሁኔታ የከተማው አስተዳደር ካቢኔ መስጠቱ ይታወሳል። ነገር ግን ደረጃውን ጠብቀው ለቀረቡት ‹‹በምደባ ይሰጠን›› ለሚሉ በርካታ ጥያቄዎች እስከ አሁን ምላሽ የለም።) እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ በከተማው አስተዳደር አማካኝነት ለነባር ይዞታዎች ለባሕረ ጥምቀት ቦታዎች ጥቂት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቢሰጥም ከ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ወዲህ ቤተ ክርስቲያን በሕጋዊ መንገድ ለያዘቻቸው ይዞታዎች ማረጋገጫ ካርታ ማግኘት አልተቻለም።

በመመሪያ ቁጥር ፩/፲፱፻፺ ላይ በምደባ የአምልኮት ቦታ ለመስጠት በተቀመጠው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተደጋጋሚ ከወረዳው እስከ የከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ጥያቄ ብታቀርብም አንድም ቦታ በምደባው መሠረት ተሰጥቶ አያውቅም።

ተደጋጋሚው የምእመናን ሕጋዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ አለማግኘቱ፣ ከከተማው መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሃይማኖት ተቋማት ጥያቄ ታሳቢ አለመደረጉና ከማስተር ፕላኑ ጋር በማጣጣም የሃይማኖት ተቋማት መገንቢያ ቦታ አለመዘጋጀቱ የአስተዳደሩ ጉልህ ድክመት ነው።

ቀድሞ የአምልኮ ማካሄጃ ቦታዎችን በማዘጋጀት ፍትሐዊነትን በተግባር በማሳየት እና በሕጉ መሠረት የሚያቀርቡለትን ጥያቄዎች በአግባቡ በፍጥነት መልስ በመስጠት የሃይማኖት ተቋማትን ማገዝ ተቀዳሚ ተግባር ቢሆንም መሬት ላይ የሚታየው ግን በተቃራኒው ነው። በሃይማኖት ተቋማት መካከል የሚታየው አላስፈላጊ ፉክክር የተፈጠረውም ሕጋዊው መመሪያና አሠራር ስለ ተገፋ ነው። የከረሙና የተጠራቀሙ ሕጋዊ ጥያቄዎችን አለመመለስም የሕዝብን ኃላፊነት አለመወጣት መሆኑንም የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ያምናል።

በተለይ የአዲስ አበባ አስተዳደር በ፲፱፻፷ ዓ.ም. ባወጣው መመሪያ ቁጥር ፩/፲፱፻፷ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን ቦታዎቹን የመጠቀም መብቱን ሰጥቶ ባለ ይዞታነቷን ግን ነጥቆ ቆይቷል።

በመመሪያው መሠረት ቤተ ክርስቲያን የባለ ይዞታነት መብቷ በመገደቡ ምንም ዓይነት ግንባታ ማከናወን ባለመቻሏ በከተማ ውስጥ የሚገኙ በርካታ የጥምቀት ማክበሪያ ይዞታዎች ለስፖርት ማዘውተሪያነት ካርታ ወጥቶባቸው ከቤተ ክርስቲያን ተነጥቀዋል።

## የሃይማኖት ተቋማት እና መመሪያው

የሃይማኖት ተቋማት የአምልኮ ማካሄጃ ቦታ ማግኘት መብታቸው ሲሆን መንግሥት ደግሞ ሕግ እና መመሪያን በመከተል ቦታ መስጠት ግዴታው ነው፡፡ የሃይማኖት ተቋማት መንፈሳዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳቸው ለጥያቄ ባይቀርብም በሁሉም ተቋማት እየተስተዋለ ያለውን ከአምልኮ ማካሄጃ ቦታ ግንባታ ጋር ተያይዞ የፉክክር እና የእልህ ጉዞን መንግሥት ሕግ እና መመሪያን በቁርጠኝነት በመተግበር ሊገታው ይገባል፡፡

መመሪያ ቁጥር ፩/፳፻፲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንቦት ፳፻፲ ዓ.ም. ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እንኳን የሃይማኖት ተቋማት የአምልኮ ቦታ ግንባታን በተመለከተ መሬት ላይ ያለው እውነታ የሚያሳየን ከመመሪያው በተቃራኒው ነው፡፡ መንግሥት መመሪያውን ለመተግበር ለምን ቁርጠኝነቱን አጣ? የሃይማኖት ተቋማቱስ የመንግሥት መመሪያን የመተግበር ውስንነትን ታከው ማኅበራዊ አለመረጋጋትን እያጎሉ የሚሄዱት እስከ መቼ ነው?

በሁሉም የሃይማኖት ተቋማት በዘፈቀደ የአዲስ ግንባታ እና ነባር መኖሪያ የነበረን ቤት ወደ ሃይማኖት ተቋምነት የመቀየር ፍላጎት ሳቢያ በየሰፈሩ እየተፈጠሩ ያሉትን አለመግባባቶች መንግሥት አያውቃቸውምን? ዝምታው ምን እስኪሆን ነው? ተቋማቱስ በፉክክር ወዴት እየሄዱ ነው? ይህ ተግባር በእንጭጩ ካልተቀጨ ወደ ከፉ ግጭት እንዳያመራ ሥጋት አለን፡፡

## የመፍትሔ ሐሳቦች

፩. መመሪያውን በቁርጠኝነት መተግበር - እስከዛሬ የነበረበትን ቸልተኝነት በመገምገም መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ካለ መድሎ መተግበር እንዳለበት እናምናለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ወደ አንድ የእምነት ተቋም የሚያደሉና ሌላውን የሚበድሉ ወገንተኛ ሰዎችን ከቦታው ማንሣት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ባይሆን እንኳን ቁጥጥሩን በማጥበቅ መመሪያውን በቁርጠኝነት መተግበር ለነገ የማያድር እርምጃ መሆን ይገባዋል፡፡

፪. የቤተ ክርስቲያናችንን ይዞታ በከተማ ፕላን ማዘመን፣ መንግሥት የአንድ ከተማን ማስተር ፕላን ሲሠራ የሃይማኖት ተቋማትን ይዞታዎች ሊዘነጋቸው አይገባም፡፡ ከዚህ ቀደም በነበሩት የከተማ ማስተር ፕላኖች በተለየ መልኩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተጎድታለች፡፡ ይህ እያደር የሚወልደው ቁጭት ለሀገር ሰላም መደፍረስም ምክንያት ሊሆን ይችላልና መንግሥት ሊያስብበት ይገባል፡፡

የሃይማኖት ተቋማት ማኅበራዊ ትስስርን እና በከተማ ዕድገት ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዲያጎለብቱ ማካተት የመንግሥት ኃላፊነት ሊሆን ይገባዋል፡፡

## የማጠቃለያ ሐሳቦች

፩. ለሀገር ግንባታ፣ አንድነትና ነፃነት ከየትኛውም አካል የበለጠ አስተዋጽዖ በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚያክል የለም፡፡ በየዘመናቱ በሀገራችን ላይ የተከሰቱ አደጋዎችን ከምእመናኗ ጋር እየመከተች መልሳ ሀገርን ገንብታለች፡፡ ሀገርን ሊጎዱ በመጡት ተጎድታለች፡፡ እርሷን ሊጠቅሙ የመጡም ሀገሪቱን ጠቅመዋል፡፡

ቢዘረዝር የማያልቅ ብዙ ሀገራዊ አበርክቶ ያላትን ቤተ ክርስቲያን፡ ከምንም አንሥታ ባቆመቻት ሀገር መግፋትና ማግለል ተገቢ አይደለም፡፡ አስተምህሮዋና ምእመናኗ ላይ ከሚደረገው ጫናና በአንዳንድ አካባቢም ከሚፈጸመው ግልጽ መድሎ ባለፈ፡ እስከ ይዞታዎቿ ድረስ መጥቶ መንጠቅና መግፋት አማኙን ሁሉ የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ተግባር ነው፡፡ ከጠላት ጠብቃና ተከላክላ በቆየችው መሬት ከተቻለ ተጨማሪ ሰጥቶ መሸለም እንጂ ያላትን ይዞታ መንጠቅ ያጎረሰ እጅን መንከስ ነው፡፡

፪. መንግሥት የከተማ አስተዳደሮች፣ ወረዳዎች፣ ዞኖችና ክልሎች ካለ አግባብ መልስ ሳይሰጡ የቆዩባቸውን የቤተ ክርስቲያን ጥያቄዎች በሕግ አግባብ መልስ የሚሰጡበትን መንገድ መቀየስ አለበት፡፡ ካለ አግባብ የተነጠቁ የቤተ ክርስቲያን ቦታዎችም መመለስ ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ካለ ወንጀላቸው ለተከሰሱ፣ ለተጎዱና ለተሠዉትም ተገቢው ካሳ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል፡፡

፫. የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር አካላት እስካሁን ከደረሰው ጥፋትና ኪሳራ ሊማሩ ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን የሚያስከብር፣ በጉዳዩ ላይ ከመንግሥትም ሆነ ከየትኛውም አካል ጋር ሊወያይና ተከራክሮ ሊያሳምን የሚችል፡ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በመዋቅር የታወቀ አካል ሊኖር ይገባል፡፡

**የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር አካላት እስካሁን ከደረሰው ጥፋትና ኪሳራ ሊማሩ ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን የሚያስከብር፣ በጉዳዩ ላይ ከመንግሥትም ሆነ ከየትኛውም አካል ጋር ሊወያይና ተከራክሮ ሊያሳምን የሚችል፡ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በመዋቅር የታወቀ አካል ሊኖር ይገባል፡፡**

፬. አንድ ባሕረ ጥምቀትን በጋራ የሚጠቀሙ አብያተ ክርስቲያናት፡ ቦታውን በዓመት አንዴ ተጠቅሞ ቸል ከማለት ይልቅ በዘላቂነት የሚጠቀሙበትን መንገድ መቀየስና መተግበር አለባቸው፡፡ ባሕረ ጥምቀቶች ሃይማኖታዊ ጉባኤያት የሚዘጋጁባቸው፣ ወጣቶችና መንፈሳዊ ማኅበራት የሚሰባሰቡባቸው፣ ሥልጠናዎች የሚሰጡባቸውና ሌሎችም መንፈሳዊ አገልግሎቶች ዓመቱን ሙሉ የሚከናወኑባቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ለዚህ ኃላፊነት ደግሞ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ የየአካባቢው ወጣቶችና ምእመናን እንዲሁም መንፈሳዊ ማኅበራት ከየቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ጋር በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

፭. የቤተ ክርስቲያን ምእመናንና አገልጋዮች በተለይ በቤተ ክርስቲያን ላይ ለሚሆነው ነገር ንቁ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመጠበቅ ዘወትር የተዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ እንደ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን በመጠቀም ከወረዳ ጀምሮ ለመምራት የሚያስብ አካል ቤተ ክርስቲያንን የማይገፋ መሆኑን ከመምረጣቸው በፊት መመርመር ይገባቸዋል፡፡

✞ ✞ ✞

# የጨቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም

*በዲ/ን ደረጄ ጋረደው*

## መግቢያ

በቅዱስ መጽሐፍ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤዶም ገነት አኖረው" (ዘፍ.፪፥፲፭) ተብሎ እንደተጻፈ ሰው ቦታን ይቀድሳል። በአንጻሩም ሰዎች በቦታ ይቀደሳሉ። ይልቁንም የቅዱሳን የጸሎት በዓታቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያለበት፣ የቅዱሳኑ አጽማቸው የረገፈበት ስለሆነ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን ያድለናል። ይህንም መሠረት በማድረግ የጨቢ መካነ ሕይወት በዓታ ለማርያም የአንድነት ገዳም ከምሥረታ እስከ አሁን ያለውን ታሪክ ለአንባብያን ልናስተዋውቃችሁ ጀመርን መልካም ንባብ።

## ፩. የገዳሙ መገኛ ቦታ፡-

መካነ ሕይወት ጨቢ በዓታ ለማርያም አንድነት ገዳም የሚገኘው በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት በዱግዳ ቦራ ወረዳ ሀርቦ አቡና ቁሙሮ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ እስከ ኬላ ከተማ ድረስ ፻፲፫ ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው ሲሆን፤ ከኬላ ከተማ ገዳሙ ድረስ ደግሞ ያለው ጥርጊያ መንገድ ፲፭ ኪሎ ሜትር ይሆናል።

"ጨቢ" ማለት በኦሮሚኛ በረከት ማለት ሲሆን፤ የገዳሙ አካባቢ ደግሞ አቡኖ በመባል የሚጠራ ነው። ይህንንም ስያሜ ያገኘበት ምክንያት በጥንት ጊዜ ቦታው ላይ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያረፉበት በመሆኑ እንደሆነ የገዳሙ አባቶች ያስረዳሉ።

ከገዳሙ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ በተራራ የተከበበ እና የተለያዩ ዕፅዋቶች የሚገኙበት ሲሆን፣ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ያለበት ሜዳ እና ገደላማ ነው። በገዳሙ አካባቢ የሚኖሩ ምዕመናን የሶዶ ጉራጌ ሲሆኑ፤ መለያ ስማቸው ግን ሶዶ ክስታኔ በመባል ይታወቃሉ። ይህንንም ስያሜ ያገኙት በጣሊያን ጊዜ በመስቀን ጦርነት ከአርሲ ሙስሊሞች ጋር ተዋግተው ብዙዎች ሰማዕትነት ተቀብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜም ሃይማኖታቸውን ሳይቀይሩ ፀንተው የቆዩ ክርስቲያኖች በመሆናቸው ነው።

## ፪. የገዳሙ አመሠራረት

መካነ ሕይወት ጨቢ በዓታ ለማርያም አንድነት ገዳም የተመሠረተው በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ነው። መሥራቹም የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የሆኑት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሣልሳዊ ናቸው። አሁን እየተጠራበት ያለውን ስያሜ ያገኘው ግን ሰኔ ፴/፲፱፻፺፰ ዓ.ም ነው። ዛሬ የሚታየው ልማት ከመምጣቱና ከመስፋፋቱ በፊት ቦታው ጠፍ እና ምንም የሌለበት የእርሻ መሬት ነበር። በወቅቱ ፫ እናቶች እና ሁለት አባቶች በጊዜው ቡታጅራ ማረሚያ ቤት ለእስር ከተዳረጉ እና የእስር ጊዜቸውን ጨርሰው በነጻ ከተለቀቁ በኋላ ወደ ሥፍራው በማቅናት አከባቢውን ሲቃኙ አስቀድሞ ቦታው ለእግዚአብሔር ማደሪያ የተመረጠ መሆኑን በመረዳት በእኒሁ አባቶች እና እናቶች ተነሣሽነት በብፁእ አቡነ ጎርጎርዮስ ሣልስ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መልካም ፈቃድ የመሠረት ድንጋይ ተቀመጠ። ለሐሳቡ እውን መሆን አቶ አማረ ዱቤ የሚባሉ የአከባቢው ነዋሪ እና የሀገር ሽማግሌ የሆኑ የአባቶችን ሐሳብ በመቀበል የራሳቸውን የእርሻ መሬት ለቤተ ክርስቲያኑ በመስጠት አሁን ያለችው የቤተ ክርስቲያን መቃኞ ሰኔ ፲፭/ ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ተጀምሮ በ፮ ወር ታንጾ ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ተጠናቆ ቅዳሴ ቤቷ ተከበረ።

በተለይ አሁን ያሉት የገዳሙ አበ ምኔት መ/ር አባ ተ/ሥላሴ በሳል የአመራር ሰጪነት በአባ ገ/እግዚአብሔር እና አባ ኃ/ገብርኤል አጋዥነት የመጀመሪያ ተግባር የነበረው

የገዳሙን ይዞታ ማስፋፋት ስለነበር እስከ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ይህን ዐቢይ ተግባር በሰፊው ቀጥለውበታል፡፡ የገዳሙ ይዞታ ፹፩.፸፱ (ሰማንያ አንድ ነጥብ ሰባ ዘጠኝ) ሄክታር ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርም ተሰጥቶታል፡፡ ወደ ፊትም ይዞታን የማስፋቱ ሥራ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የእኒህ አባቶች ምኞት እና ራእይ ለትውልዱ አርዓያ የሚሆንና ለችግረኞች መጠጊያ ሊሆን የሚችል ገዳም መመሥረት በመሆኑ ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ጎን ለጎን ተግባር ቤት እና የእናቶች ማደሪያ ሠሩ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ገዳሙ፣ የገዳሙ መናንያንና ልማት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ገጽታ ሆኑ፡፡

## ፫. የገዳሙ ሥርዓተ አበው

### ፫.፩. አንድነት

ገዳሙ የአንድነት ገዳም በመሆኑ ጠንካራ የአንድነት ሥርዓት አለው፡፡ በዚህ ገዳም ቁሪት (የግል ሀብት) አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡ በገዳሙ በምናኔ የሚኖርም ሆነ በእንግድነት የመጣ ማንኛውም ሰው የገዳሙን የአንድነት ስርዓት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ ምዕመናን ወደ ገዳሙ ሲመጡ በመናንያን ላይ መሰናክል እንዳይሆኑ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡ የጠበልተኞች ማረፊያ ለብቻ የተዘጋጀ ሲሆን ወደ እናቶች ገዳም መግባት በጥብቅ ይከለከላል፡፡ ማንኛውም የማኅበር አባል ለግል ጉዳይ በልዩ ልዩ ምክንያትና ችግሮች ወደ ሌላ ቦታ ደርሶ ለመመለስ ያሰበ እንደሆነ አስቀድሞ መምህሩን ወይም መጋቢውን ወይም ሊቀ አርድዕቱን ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡ መናንያን ፫ ዓመት እና ከዚያ በላይ ገዳሙን ካገለገሉ በየዓመቱ በገዳሙ ወጪ ተሸፍኖላቸው ታሪካዊ ገዳማት በመጎብኘት ከበረከት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ ለእናቶችም ወርኃዊ የንጽሕና መጠበቂያ በወቅቱ ይሟላላቸዋል፡፡ ከአቅም በላይ ከሆነ ግን ወደ ገዳሙ አስተዳደር ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

### ፫.፪. ሥርዓተ ምንኵስና

ወደ ገዳሙ ለመግባት የሚፈልጉ መናንያን በገዳሙ ሕግና ሥርዓት መሠረት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ሆኖ በሃይማኖቱ ሕጸጽ የሌለበት፣ በገዳሙ ደንብ ለመተዳደር ፈቃደኛ የሆነ፣ ከመጣበት አካባቢ ማንነቱን የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡ ከሌላ ገዳም የሚመጣ መናኒ የማኅበሩ አባል ለመሆን ሲያመለክት ከመጣበት ገዳም በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ አንድ የማኅበር አባል የገዳም ፈሪነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ወረቀት ሚያገኘው በገዳሙ ውስጥ አባል ሆኖ ቢያንስ አንድ ዓመት የቆየ እንደሆነ ነው፡፡ በአሁ ጊዜ በገዳሙ ተገኝተን በተመለከትነው መረጃ በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ መናንያን አባቶች ፲፱ እናቶች ፲፮ በአጠቃላይ ፴፭ ናቸው፡፡

### ፫.፫. ሥርዓተ ጸሎት


- ✞ በገዳሙ የጸሎት ሥርዐት በቀን ሰባት ጊዜ የሚጸለይ ሲሆን፤ እነዚህም በመዓልት በ፫፣ በ፮፣ በ፱፣ በ፲፩፣ በሌሊት በ፫፣ በ፮፣ በ፱ ናቸው፡፡
- ✞ ዘወትር በጠዋት ኪዳን ይደረሳል፡፡
- ✞ መነኰሳይያት የማታ ጉባኤ እና ትምህርት አላቸው፡፡

### ፫. ፬. አመጋገብ እና የአለባበስ ሥርዐት

በገዳሙ መናንያን ከሰኞ እስከ ዓርብ በሁለት ቀን አንድ ጊዜ በ፱ ሰዓት፣ ቅዳሜ እና እሑድ በ፫ ሰዓት አንድ ዳቤ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ በሥራ ላይ ለሚሰማሩት ግን በየቀኑ ምሳ ላይ እንጀራ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአብነት ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ እንጀራ ይሰጣቸዋል፡፡ መናንያኑ የሚለብሱት ሁሉም አንድ አይነት የሆነ እና በገዳሙ መናንያን ከቅጠላቅጠል በሚዘጋጅ ቀለም የሚነከር ቀይ ቡኒ ቀለም ያለው አቡጀዲ ሲሆን፤ አሰፋፉም የገዳማውያንን ሥርዓት የተከተለ ነው፡፡



የገዳሙ መናንያን እና አለባበስ በከፊል



የገዳሙ መናንያን እናቶች በበዓል ጊዜ

### ፲.፭. የቅጣት ሥነ ሥርዐት

በአጋጣሚ በመናንያን መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በራሳቸው እንዲፈቱ ይደረጋል። ነገር ግን ከገዳሙ ሥርዐት የወጣ መናኒን እንደ ጥፋቱ መጠን የተለያዩ ቅጣቶች ይሰጡታል። እነዚህም የጉልበት ሥራ (እንጨት ለቀማ፣ ፅዳት እና የመሳሰሉት)፣ ስግደት፣ በእግር ብረት መታሰር ሲሆኑ፣ ከነዚህም ቅጣቶች ጎን ለጎን ተግሣፅ እና ምክርን ያካትታል።

## ፲፩. የገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር

ገዳሙ መናንያን የሚመሩበት የራሱ የመተዳደሪያ የውስጥ ደንብ አለው። በመዋቅር ደረጃ ከገዳሙ አስተዳደር መምህር ጀምሮ የምርፋቅ አባቶች፣ ጸሐፊ፣ መጋቢ፣ ሒሳብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥ፣ ኦዲተር፣ ዕቃ ግዢ ኃላፊ፣ ዕቃ ቤት ጠባቂ የሚል መዋቅር ተበጅቶለታል። የውስጥ ደንቡ የገንዘብ እና የዕቃ ወጪ አጠባበቅ፣ የገዳሙ ሥራና ሊቀ አርድዕቶች፣ ስለ ገዳሙ ፀጥታ አጠባበቅና ቅጣት፣ የአዲስ አባላት አቀባበል፣ ወደ ገዳሙ ስለሚመጡ እንግዶች፣ ስለ ሴቶች ገዳም፣ ስለ ገዳሙ አርድዕቶች፣ ስለ ሕመምተኞች፣ ደካሞችና ባሕታውያን፣ ስለ ውርስ ገንዘብ፣ ስለ ልማት፣ ስለ ትምህርት፣ ስለ መቁነንና የዓመት ልብስ፣ ስለ ስብሰባ፣ ስለ ፈቃድ፣ ስለ ጸሎተ ማኅበር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ አቤቱታ ስለማቅረብ፣ ስለ ሥራና ዕቅድ ግምገማ፣ ስለ ሥራ ሪፖርት፣ ስለ ግል ቁሪት (የግል ሀብት)፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች ገዳም ክልል፣ ስለ ገዳሙ ተጠሪነት በስፋት ያብራራል።

## ፲፪. የአብነት ትምህርት ቤትና ስብከተ ወንጌል

የአብነት ትምህርት ቤቶች ለገዳማት ህልውና ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው በገዳሙ በመታመኑ ቀዳሚ ቦታም ተሰጥቶታል። የሁለት ጉባኤያት መምህራን የተቀጠሩ ሲሆን እነዚህም የአቋቋም እና የቅዳሴ መምህራን ናቸው። የቅዳሴ መምህሩ በማኅበረ ቅዱሳን አጋዥነት ከአካባቢው ሁለት ሰዎች በመላክ የደብረ አባይ ቅዳሴ አስመስክረው የመጡ ሲሆን አንደኛው በገዳሙ ወንበር ዘርግተው በርካታ የአካባቢውን ተማሪዎች እና መናንያንን እያስተማሩ ይገኛሉ። ገዳሙ እየታወቀ ሲመጣ የአቋቋም ተማሪዎችም እንደሚኖሩ ገዳሙ ተስፋ አለው። የአብነት ተማሪዎቹ ቀለብ በገዳሙ የሚሸፈን ሲሆን የማደሪያና የጉባኤ ቤት ችግር ግን አንዱ ፈተና ነው። ችግሩንም ለመፍታት ገዳሙ የተማሪዎች ማደሪያና የጉባኤ ቤት ዲዛይን ያሠራ ሲሆን በምእመናን ድጋፍም ግንባታው እንደሚሠራ ይታመናል።

አንዳንድ የማኅበሩ አባላት የተሟላ ገዳማዊ ጠባይ እንዲኖረው ቅዳሜና እሑድ እንዲሁም በየዓመት በዓሉ ስብከተ ወንጌልና የመጻሕፍት መነኮሳት ትምህርት በገዳሙ ውስጥ እንዲሰጥ ይደረጋል።



የገዳሙ የአብነት ተማሪዎች

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

*ክፍል ሁለት*



*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*



መምህር ሥሙር አላምረው

***ዲ. ሐመር፡-*** ‹‹ሰው አምላክ ሆነ አምላክ ሰው ሆነ›› ስንል ከላይም እንደ ተገለጸው ልዑለ ባሕርይ መለኮት ትሑቱን ሥጋ ገንዘብ አደረገ ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ "ሁሉ ተካክሎ በደለ አንድ ስንኳን በጎ ነገርን የሚያደርጋት የለም" (መዝ.፲፫፥፫፤ መዝ.፶፪፥፫) እንዳለ አንድም ንጹሕ ሰው አልነበረም፡፡ ስለዚህ ‹አምላክ የተዋሐደው ሥጋ ጥንተ አብሶ ነበረበት› አያስብልም ወይ?

***መምህር ሥሙር፡-*** እዚህ ላይ መጠንቀቅ የሚያስፈልገው ነገር "ሁሉ" የሚለው ቃል አንጻራዊ ነው፡፡ ለምሳሌ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" (ሉቃ.፩፥፵፰) ብላ ስትናገር አንጻራዊ በሆነ አገላለጽ እንጂ የማያምን እንዳለ የታወቀ ነው፡፡ ሁሉ የሚለው ቃል አማኞችን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ዳዊት የተናገረው ቃል በተነገረበት ዘመንና ከተነገረበት ዘመን በፊትም የነበረውን ብንመለከት ሁሉም አልበደሉም፡፡ ለምሳሌ፡-

በብሉይ ኪዳን ጽድቅ የመርገም ጨርቅ ቢሆንም እጅግ በርካታ ደጋግና ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ ነበሩ መዘንጋት የለብንም፡፡ በዘፍ.፬ ስለ አቤል ጽድቅ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ሄኖክ እንደ ተሰወረ እናገኛለን፡፡ ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት "አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" (ዘፍ.፲፩፥፮)ተብሏል፡፡ እንደ አብርሃም ያሉ ጻድቃን እንደ ይስሐቅ ያሉ ታዛዦች፣ እንደ ያዕቆብ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ የነበረው በ፶፻፭፻ ዘመን ውስጥ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉ በደለ ከተባለ በሕገ ልቡናም ሆነ በሕገ ኦሪት ብዙ ደጋግ ሰዎች ነበሩና ከመሆናቸው ጋር ይጋጫል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የሚለው ቃል በደለኞችን ብቻ እንጂ ያልበደሉትን አይጨምርም፡፡

ነገሩን በተሻለ መልኩ ግልጽ ለማድረግ እግዚአብሔር አምላካችን ስለ ዳዊት ሲናገር "ኢይጠፍእ ምስፍና ወምልክና እምአባሉ ለይሁዳ፤ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ ምስፍናም ከአብራኩ" (ዘፍ.፵፱፥፲) በሚለው እኮ ለዘለዓለም አይጠፋም ተብሎ ተነግሮ ግን ጠፍቷል፡፡ በእስራኤል ዘንድ አሁን በዘመናችን እንኳ ጥንት በተነገረው መንገድ አይደለም፡፡ በሀገራችንም ቢሆን የዳዊት ዘር ነን የሚሉ የነበሩበት ዘመን እንደ ነበር ቢታወቅም በየመሀሉ እጅግ የተቆራረጠበት ዘመን ነበር አሁንም በዚያ መንገድ የለም፡፡ ስለዚህ አንጻራዊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ስለ ዳዊት የተነገረው ለዘለዓለም የሚለው ቃል የዳዊትን ልጆች ብቻ የሚመለከት እንደ ሆነ ሁሉ "ሁሉ ተካክሎ በደለ" የሚለውም በደለኞችን ብቻ እንጂ ሁሉንም አይመለከትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምንም በራሳቸው ቅዱሳን ቢሆኑም

ጽድቃቸው እንደ መርገም ጨርቅ ሆኖባቸው ወደ ገነት መግባት አልቻሉም ነበር፡፡ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ ነፍሳት እስካዳነበት ጊዜ ድረስ ሁሉም የሲኦል እስረኞች ነበሩ፡፡

በሌላ መልኩ በቀጥታ ወደ ተነሣው ጥያቄ ስንመለስ ልናየው የሚገባው ነገር እመቤታችን ከእነዚህ ንጹሐን ከምንላቸው ሁሉ በተለየ ሁኔታ ንጽሕት ናት፡፡ ሌሎቹ ጻድቃን ቢባሉም የአዳም መርገም አይጠፋባቸውም፡፡ በራሳቸው ንጹሐን ቢሆኑም የራሳቸው ንጽሕና ገነት መንግሥተ ሰማያት ስለማያስገባቸው የሲኦል እስረኞች ነበሩ፡፡ የራሳቸው ንጽሕና የራሳቸው ብቃት የገነትን በር ሊከፍትላቸው ስላልቻለ በአዳም መርገም ምክንያት የገነት በር ተዘግቶባቸዋል፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የአዳም መርገም በውስጧ ስለሌለ ከሁሉም የተለየች ናት፡፡ ቴዎዶጦስ የተባለ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ "ወኢረኰሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ፤ ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምን አልረከሰችም" (ሃ. አበው ፶፫፥፳፱) በማለት ይነግረናል፡፡ ይህ ቃል ሲብራራ አዳም ከወደቀበት በፊት የነበረውን ቅድስና ይዛ ኖራለች ማለት ነው፡፡ "ወበከመ ነፍሀ ውስተ ገጹ ለአዳም ከማሁ አንቲኒ ሀሎኪ ወኢረሳህኪ፤ አዳም ከመውደቁ በፊት ንጽሐ ጠባዕይ ሳያድፍበት እንደነበር አንቺም እንደዚያ ነሽ" እንዲል፡፡ አዳም በተፈጠረበት ቅጽበት ያገኘውን ጸጋ ይዞ ሰባት ዓመት ይዞት የነበረውን ንጽሐ ጠባዕይ ሳታሳድፍ ይዛ የተገኘች ናት፡፡ ይህ ከፍጥረት የምትለይበት አንዱ መገለጫዋ ነው፡፡

ስለዚህ ሁሉ በደለ የሚለው ቃል እመቤታችንን አይመለከትም፡፡ እግዚአብሔር የጠበቃት ንጽሕት ናት፡፡ "መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ፤ ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠብቋታልና" ከአባት ወደ ልጅ የሚመጣው መርገም የለባትም፡፡ ስለዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ጥንተ አብሶ የለበትም፡፡

እመቤታችን ከጥንተ አብሶ ንጹሕ መሆኗን ለማስረዳት ተጨማሪ ምሳሌ ብንጠቅስ ጌዴዎን አሕዛብን ድል ታደርጋለህ ሲባል እርሱ ‹‹እንዴት እችላለሁ›› ብሎ ተከራክሮ ነበር፡፡ በዚህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው ተባለ፡፡ እመቤታችንን ግን መልአኩ ሲያበሥራት እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው ብቻ አላላትም፤ ‹‹ጸጋን የተመላሽ ነሽ›› የሚለውንም ልዩ ቃል ተናግሯል፡፡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የነበሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ ጸጋን የተመሉ ግን አልነበሩም፡፡ ስለዚህ በጨለማ ዘመን ጸጋን የተመላች፣ ከተፈጠረች ጀምሮ ንጽሕት የሆነች፣ የእናት የአባት መርገም ካለባቸው እናት አባት ተገኝታ እርሷ ግን መርገም ያላገኛት ንጽሕት ዕንቊዕ ከአዳም አብራክ ጀምራ የምታበራ ሁና ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ከፍጥረታት ሁሉ የተለየች ስለ ሆነች ጥንተ አብሶ የሚባል ነገር አያውቃትም፡፡ በመሆኑም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋም ከጥንተ አብሶ የነጻ ነው፡፡

***፮. ሐመር፡-*** "ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሣ" ስንል ምን ማለታችን ነው?

***መምህር ሥሙር አላምረው፡-*** ይህን በአጭሩ በሁለት መንገድ እንመልከተው፡፡ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሣ ስንል "ከ" የሚለውን በትኩረት መመልከት የተሻለ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ እመቤታችንን ‹ሥጋዋን ነፍሷን ነሣ› ማለትና ‹ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሣ› ማለት እጅግ የተለያዩ ናቸው፡፡ ሥጋዋንና ነፍሷን ነሣ ብንል ራሷን እመቤታችንን ተዋሐደ ማለት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ እርሷም አምላክ ሆነች ያሰኛል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር እናት ሳይሆን እግዚአብሔር ናት ወደ ማለት ይወስደናል፡፡ እንዲህ እንዳይሆን ከሥጋዋ ከፍሎ ከነፍሷም ከፍሎ ተዋሐደ ማለት እንጂ እርሷን ተዋሐደ ማለት አይደለም፡፡

አምላክ ሰው የሆነው ከነፍሷ ነፍስን ከሥጋዋ ሥጋን ከፍሎ ነው፡፡ ሰው ከእናቱና ከአባቱ ከፍሎ የሚነሣው አለ፡፡ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮም ሰው ሲወለድ ከአባቱ ዘርን ከእናቱ ደምን ነሥቶ ነው፡፡ ይህ የአባት ዘር በክርስቶስ ዘንድ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ከፍሎ ተዋሐደ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ "ህየንተ ነፍስ ኮኖ መለኮቶ፤ በነፍስ ፈንታ መለኮቱ ነፍስ ሆነው እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም" የሚሉ መናፍቃን ለምሳሌ እንደ አቡሊናርዮሳውያን ያሉ አሉ፡፡ ለእነዚህ በአጭሩ መልስ የሚሆነው የእነ ሳዊሮስ መልስ

ነው፡፡ ሳዊሮስ እንዲህ ብሎ ይጠይቃል "እኛ ክርስቶስ በሥጋ ሞተ እንላለን በሞተም ጊዜ ነፍሱ ወደ ሲኦል ወረደ፤ ሥጋው በመቃብር ነበር እንላለን፡፡ እናንተ ነፍስን አልነሣም የምትሉ ከሆነ መለኮት ከሥጋ ተለይቶት ነበር፡፡ ያንጊዜ ወደ ሲኦል የሄደው ከሥጋ ጋር አልነበረም ማለት ነውን? እንዲህ ከሆነ ሩቅ ብእሲ ነው ያስብላል፡፡ ዕሩቅ ብእሲ ከሆነም ውላጤ ያለበትን አምላክ እንዴት ልናመልከው እንችላለን?" በማለት ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ ቤዛነትን አያመጣም፡፡ እንዲህ ዓይነት በተከፍሎ አንድ ጊዜ አምላክ ሌላ ጊዜ ሰው የሚሆን መለኮት የሚለየው እንደ ገና የሚዋሐደው ከሆነ ቤዛነታችንም ፍጹም አይሆንም፡፡ ነገር ግን ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያስረዳን መለኮት ሥጋንም ነፍስንም ተዋሐደ የሚለው ነው፡፡

በሌላ መልኩ ምሥጢረ ሥጋዌን ይንደዋል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ‹ሰው ነው› የሚባለው ነፍስም ሥጋም ሲኖረው ነው፡፡ ከዚያ ውጭ በደማዊት ነፍስ እንስሳ ነው የሚሆነው፡፡ በደማዊት ነፍስ ደግሞ እንስሳትም ሕይወት አላቸው፡፡ ክርስቶስ ግን እንዲህ እንዳልሆነ "ወኢኮነ ካልዐ እንስሳ ዘበአንትጎ አላ ምሉዕ ውእቱ ወፍጹም ምስሌነ ዘበ ሕላዌ፤ በማጉደል ሌላ እንስሳ የሆነ አይደለም፡፡ በሕልውና ከእኛ ጋር ምሉዕና ፍጹም ነው እንጂ" (ሃ.አበው ዘቅዱስ ኤፍሬም ፺፯፥፴፪) እንስሳት በደም ሙቀትና በደም ዝውውር ሕይወት አላቸው እንጂ ሕያዊት ነፍስ የላቸውም ፡፡ ክርስቶስ አምላካችን ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ ስለዚህ ነፍስንም ሥጋንም ባይነሣ ፍጹም ሰው ልንለው አንችልም፡፡

***፮. ሐመር፡-*** እግዚአብሔር ሰማይና ምድር የማይወስኑት አምላክ ነው፡፡ ግን አንዲት ብላቴና ወሰነችው፤ እንዲህ ከሆነ ማለትም በአንዲት ብላቴና የሚወሰን ከሆነ አምላክ ነው ማለት እንዴት እንችላለን?

***መምህር ሥሙር አላምረው፡-*** ይህ የአባ ሕርያቆስም ጥያቄ ነው፡፡ አባ ሕርያቆስ "መንበር ኪሩባዊ ዘያንጸበርቅ ወዘየዐውዶ ነደ እሳት አይቴኑ ተደለወ ወአይቴኑ ተተክለ  በውስተ ከርሥኪ እንዘ ንእስት መርዓት አንቲ፤ የሚያንጸበርቅ ነደ እሳት የሚከበው ኪሩቤል የተሸከሙት ዙፋን በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተተከለ? አንቺ ታናሽ ሙሽራ ስትሆኚ" (ቅዳሴ ማርያም) እንዲል፡፡ አባ ሕርያቆስ ጠይቆና አድንቆ ብቻ አልቀረም፡፡ እልፍ ይልና "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እንበል" ብሎ ከዚህ በላይ ሊባል እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ በእርግጥ ሊቃውንቱንም እጅግ ያስደነቃቸው እንዲህ ያለው ልዩ ምሥጢር ነው፡፡

ከላይም እንደ ተገለጸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም እንዲህ ያለውን ምሥጢር ሲያደንቅ "ለቀዳማዊ ልደት አመሥጠሮ ወለደኃራዊ ልደት አመንከሮ፤ የመጀመሪያውን ልደት ረቂቅ አደረገው ሁለተኛውን ልደት ደግሞ ድንቅ አደረገው" (መጽሐፈ ምሥጢር) በማለት ያስረዳል፡፡ እጅግ ድንቅ የሚያደርገው በዓለም ሁሉ ምሉዕ የሆነ መለኮት በዓለም ምሉዕ ካልሆነች አንዲት ብላቴና ማኅፀን ተወስኖ ማደሩ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተወሰነ ስንል መላእክትን ሳይቀር እንዳስደነቀ በታች በምድር በእመቤታችን ማኅፀን ሆኖ ያዩታል፤ ቀና ሲሉ ደግሞ በላይ በሰማይ በኪሩቤል ዙፋን ተቀምጦ ያዩታል፡፡ እዚህ በእመቤታችን እቅፍ ያዩታል በላይ በሰማይ ደግሞ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ዕሪና ሳይለይ የኪሩቤልን ምስጋና ሲቀበል ያዩታል፡፡ ስለዚህ ተወሰነ ስንል በዚህ መንገድ እንጂ የሰማይ ዙፋኑን ትቶ፣ ምሉዕነቱን፣ አምላክነቱን፣ ወዘተ ትቶ ማለት አይደለም፡፡ እንደ ሰውነቱ ተወሰነ እንደ ምላክነቱ ደግሞ ዓለምን ሞልቷል፡፡

በሌላ መልኩ ‹ሰማይና ምድር የማይወስኑት አምላክ በአንዲት ብላቴና እንዴት ተወሰነ?› የሚለውን ሊቃውንቱ በዐይን ብሌንና በፀሐይ ብርሃን ይመስሉታል፡፡  እንደሚታወቀው የዐይን ብሌን ጠባብ ነው፡፡ የፀሐይ ብርሃን ደግሞ አንጻረዊ በሆነ መልኩ ምሉዕ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ዐይናችን ከፀሐይ ብርሃን ሙሉ በሙሉ አይቀበልም፡፡ ብርሃን የሚቀበለው የተወሰነው የዐይናችን ክፍል ነው፡፡ ይህ ግዙፍና ሰፊ የሆነው የፀሐይ ብርሃን ከጠባቧ የዐይናችን ብሌን ጋር በተዋሐዱ ጊዜ ብዙ ነገር ማየት ይችላል፡፡ የሰው ዐይን የፍጡር ዐይን በመሆኑ ጠፈር ደፈር ቢከለክለውም ብዙ ነገር ማየት ይችላል፡፡ እመቤታችን በዐይን ብሌን ትመሰላለች፡፡ መለኮት

ደግሞ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ” እንዳለ በፀሐይ ብርሃን ይመሰላል። ስለዚህ ምሉዕ የሆነው መለኮት በዐይን ብሌን ከተመሰለችው ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተዋሐደ። ምሉዕ መለኮት ተወሰነ፣ ውስኑ ሥጋ መላ እንላለን።

በመሠረቱ ተወሰነ ብቻ አይደለም የምንለው ምሉዕ መለኮት በሥጋ ማርያም ሲወሰን በኪሩቤል ዙፋን ተቀምጦ ይመሰገን ነበር። ነቢዩ ኢሳይያስ “ከዚህም በኋላ ንጉሡ ኦዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረዥምና ከፍ ባለ ዙፋን ተቀምጦ አየሁት። ምስጋናውም ቤቱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም በዙሪያው ቆመው ነበር…አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር” (ኢሳ.፮፥፩-፫) በማለት እንደ ገለጸው እግዚአብሔር በዙፋኑ ሆኖ ሳለ ምስጋናው ቤቱን (መቅደሱን) ሞልቶት ነበር ይላል።

> “ከዚህም በኋላ ንጉሡ ኦዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረዥምና ከፍ ባለ ዙፋን ተቀምጦ አየሁት። ምስጋናውም ቤቱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም በዙሪያው ቆመው ነበር… አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር”

መቅደስ የተባለችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። መቅደሱን የሚያየው በሰማይ ነው። ሰማይ ተከፍቶ በመቅደሱ ውስጥ ምስጋናው ሞልቶ ይመለከታል። በታች በምድር ደግሞ በእመቤታችን ማኅፀን ሲመሰገን ያያል። ስለዚህ እግዚአብሔር በፈቀደ ለእናትነት መርጦ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በሥጋ ተወሰነ ተባለ ይህ እጅግ የሚደንቅ ስለ ሆነ ሊቃውንቱም ዕፁብ ዕፀብ ብለውት አልፈዋል።

***ሐመር፡-*** መምህር በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?

***መምህር ሥሙር አላምረው፡-*** ነገረ ሥጋዌን በዘመናችን ሙሉ ብንናገረው እንዳልተናገርነው ይቆጠራል እንጂ ገልጸን ልንጨርሰው አንችልም። በመሆኑም ይህኛው ተባለ ይህኛው ደግሞ ቀረ የሚባል ነገር አይኖርም። ነገር ግን ምሥጢረ ሥጋዌ (ምሥጢረ ተዋሕዶ) ከትምህርተ ሃይማኖቱ በዘለለ የሰው ልጆችን ማሕበራዊ አንድነት፣ ኅብረትም የሚያስተምር ነው። ምክንያቱም በባሕርይ የማይመሳሰሉ አካላት አንዱ ሌላውን ሳያጠፋው በተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ። እንዲሁ ሰዎችም ምንም ብዙ የሚያለያዩ ነገሮች ቢኖሯቸውም አንዱ ሌላውን ሳይጎዳ በኅብረት፣ በአንድነት እንዲኖሩ የሚያስተምር ነው። ስለዚህ እርስ በእርሳችን ተቻችለን፣ ተከባብረን፣ በአንድነት ኖረን የማያልፈውን ርስት መንግሥተ ሰማያት እንድንወርስ በዚህ ልክ መዘጋጀት አለብን። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን።

***ሐመር፡-*** መምህር ጥሪያችንን አክብረው ስለ ተገኙልን፣ ላነሣናቸው ጥያቄዎችም ተገቢ ምላሽ ስለ ሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

***መምህር ሥሙር፡-*** እኔም አመሰግናለሁ፤ ማኅበሩንም እግዚአብሔር ይጠብቅልን አሜን።

✝ ✝ ✝

# ኢየሱስ ወደ ሰርግ ቤት ተጠራ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሄደ።

*(ቅዱስ ያሬድ፣ ድጓ ዘቃና ዘገሊላ)*



*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*

ጋብቻ የራሱ የሆነ ዝግጅት አለው። ይህ ዝግጅት ደግሞ ሰርግ ይባላል። ‹‹ሰርግ›› የሚለውን ቃል አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ‹‹ሰረገ፣ ደገሰ፣ ሰርግ አደረገ፣ የሰርጉን ቤት ሸለመ፣ አስጌጠ፣ አንቆጠቆጠ” በማለት ሲገልጹት አያይዘውም “ሰርግ በቁሙ፣ ከብካብ፣ መርዓ፣ የጋብቻ በዓል ድግስ፣ የሚያጌጡበት፣ የሚሸለሙበት።›› በማለት ያብራሩታል። (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ ፷፻፹፬) ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘ መጽሐፋቸው ‹‹አካለ መጠን ያደረሰ ወንድ ልጅና አካለ መጠን ያደረሰች ሴት ልጅ ባልና ሚስት ሊሆኑ የሚጋቡበት ቀንና ተጋብተውም የዚህን ዓለም ኑሮ የሚጀምሩበት የሰርግ ቀን›› (ገጽ ፪፻፴፱) በማለት ይገልጹታል። ከሁለቱም ምሁራን አገላለጽ እንደምንረዳው ሰርግ የዕለት ክንውን ሲሆን ጋብቻውን ምክንያት አድርጎ የሚደገሰውን ድግስ የሚለበሰውን ልብስ፣ የሚታየውን ጌጣጌጥ የሚያካትት የማስተዋወቂያ ዝግጅት ነው። ማለትም ሰዎች ከብቸኝነት ሕይወት ወደ ጥንድነት የሚሸጋገሩበት ዝግጅት ነው። ይህ ዝግጅት የሁለቱ አንድነት የሚታወጅበት በሁለታችንም ፍላጎት በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ለዚህ በቅተናልና የደስታችን ተካፋይ ሁኑ በማለት ሙሽሮች በሚያስተላልፉት ጥሪ መሠረት ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ የሁለቱ ተዋሕዶ የሚታወጅበት ወይም አዋጁ የሚጸድቅበት ልዩ የዝግጅት ጊዜ ነው።

ይህ የሰርግ ዝግጅት በብሉይ ኪዳንም ይከናወን እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። ያዕቆብ የላባን ልጅ ያገባ ዘንድ ወደ ለላባ ሰባት ዓመት ከተገዛ በኋላ ላባም ሰርጉን ደግሶ አጋብቶታል። ‹‹ላባም የዚያን ስፍራ ሰዎች ሁሉ ሰበሰበ ሰርግም አደረገ።›› (ዘፍ. ፳፱፥፳፪) እንዲል። ስለዚህ የሙሽሮች እናት አባት አሊያም ራሳቸው ሙሽሮች ቤተ ዘመዳቸውን፣ የአካባቢውን ሰው እና ለሰርጋቸው ድምቀት ይሆነናል ያሉትን ሁሉ ሰብስው ደስታቸውን የሚያውጁበት መጣመራቸውን የሚያሳውቁበት ዝግጅት ነው።

በሐዲስ ኪዳንም እንዲህ ያለው ሥርዐት ቀጥሏል። በዚህ ልማድ ዶኪማስ ሰርጉን አዘጋጅቶ ዘመዶቹን ጠራ። በወቅቱ ከተጠሩት ታዳሚዎች መካከል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበረ። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ቃና ዘገሊላን በአዘከረበት የድጓ ክፍሉ ይህን ሲያስረዳ “ከብካብ ኮነ ከብካብ ኮነ ወኮነ እሙነ በቃና ዘገሊላ ተጸውዐ ኢየሱስ ውስተ ከብካብ ወሖረ ምስለ አርዳኢሁ፤ በገሊላ ቃና ሰርግ ኾነ፤ ሰርግ ኾነ፤ የታመነም ኾነ ኢየሱስ ወደ ሰርጉ ተጠራ፤ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሄደ” በማለት ተናገረ።

ይህ ታሪክ በቅዱስ ወንጌልም “በሦስተኛውም ቀን የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና ሰርግ ሆነ፤ የጌታችን የኢየሱስ እናትም በዚያ ነበረች። ጌታችን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።” (ዮሐ.፪፥፩) ተብሎ ተመዝግቧል። በዚህ ምንባብ ጠሪ አለ ተጠሪ አለ ተጠሪው ከማን ጋር ሄደ የሚለውና ለምን ተጠሩ የሚለውን እንመለከታለን።

**ጠሪ፦** ጠሪው ሰርጉን ያዘጋጀው ሰው ነው። ሰርጉ ከላይ እንደ ተገለጸው የደስታ መግለጫ እንደመሆኑ ደስታን የሚካፈል ሰው ያስፈልጋል። በሰው ሕይወት ላይ ልደት እንዳለ ሁሉ ሞት አለ። ደስታ እንዳለ ሁሉ ኀዘን አለ። ስለዚህ ደስታንም ሆነ ኀዘንን በጋራ ሲያከናውኑት እጅግ ያምራል። ደስታውም ብቻን ከሆነ አያምርም፤ መደሰታችንን ዕወቁልን ብለን ስለሆነ የምንጠራው የእኛን ደስታ የሚመሰክሩ፤ የእኛን ደስታ ተመልክተው እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ፣ ከእኛም ጋር የሚደሰቱ ሰዎች መኖር አለባቸው።

በኀዘን ጊዜም ቢሆን ከኀዘናችን የሚያረጋጉን፣ ኀዘናችንን የሚካፈሉልንና የሚያጽናኑን ሰዎች ያስፈልጉናል። እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሄሮድስ የተወደደ ልጇን እንዳይገድልባት በተሰደደች ጊዜ የተናገረችውን የኀዘን ቃል ሰቆቃወ ድንግልን የጻፈልን ሊቅ አባ ጽጌ ድንግል “ አይቴ ይእቲ ሐና እምየ፤ ወኤልሳቤጥኒ እንተ እምአዝማድየ፤ ይብክያኒ ሊተ በእንተ ንግደትየ ለሐወት ማርያም እንዘ ትብል ወይልየ ዘየአምረኒ ሊተ ኃጣእኩ በዝየ፤ ሐና እናቴ

ወዴት ናት? ከዘመዶቼ ወገን የሆነች ኤልሳቤጥስ፤ ስለ ስደቴ ያለቅሱልኝ ዘንድ፤ በዚህ ቦታ የሚያውቀኝ (የሚያጽናናኝ) አጣሁ እያለች ማርያም አለቀሰች ” (ሰቆቃወ ድንግል) በማለት በኀዘን ጊዜ ሰው የሚያስፈልግ መሆኑን ያስረዳናል።

በመጽሐፈ ሲራክ “ከሚያለቅሱ ሰዎችም አትለይ፤ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅስ። ሕመምተኛንም ሰው መጎብኘት ቸል አትበል፤ በዚህም ይወዱሃል” (ሲራ.፯፥፴፬-፴፭) ተብሎ ተጽፏል። ስለዚህ በኀዘንም ሆነ በደስታ ወቅት ሰው ከጎናችን ኾኖ ከደረሰብን ኀዘን ሊያጽናናን፣ ከአገኘነው ደስታ ደግሞ ሊካፈል ያስፈልጋል። ዶኪማስም ሰርጉን ደግሶ ዘመዶቹን የጠራው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የጠራ በዚህ ልማድ ነበር።

**ተጠሪ፡-** ወደ ሰርጉ የተጠራው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በኀዘናችንም ኾነ በደስታችን አስቀድመን እርሱን መጥራት ያለብን መሆኑን ያስገነዝበናል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሊቃውንቱ ተደጋግሞ እንደተነገረው ከኃጢአት ብቻ በቀር እንደኛ ሰው ኾኗልና በኀዘን ቤትም ተገኝቶ ኀዘንተኞችን አጽናንቷል፤ ስለሞተው ስለ አልዓዛር እርሱም አልቅሷል። በዚህ ያዩት ሁሉ እንዴት ይወደው ነበር? ብለው አድናቆታቸውን ገልጸዋል። (ዮሐ.፲፩፥፳፫-፴፯)

> **“እናትን ጠርቶ ልጅን መተው ፈሊጥ አይደለምና እናታችን ቅድስት ማርያም ስትጠራ ልጇም ተጠራ። መምህርን ጠርቶ ደቀ መዝሙርን መተው አግባብ አይደለምና ጌታችን ሲጠራ ደቀ መዛሙርቱም አብረው ተጠሩ”**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ሕይወት እንደሚያስፈልገው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም አስተምሯል። በኀዘን ቤት ተገኝቶ ኀዘንተኞችን እንዳጽናና በሰርግ ቤት ተገኝቶ ባለ ሰርጉን አስደስቷል። ባለ ሰርጉ አክብሮ እንደጠራው ሁሉ እርሱም ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠሪውን አክብሮ በሰርግ ቤት ተገኝቷል። ወደ ሰርጉ የተጠሩት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መሆኑን እንረዳለን።

**ከማን ጋር ሄደ፡-** ባለ ሰርጉ መምህሩን ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠራ። ዛሬ ዛሬ የጥሪ ወረቀት ይዘጋጅና በመጨረሻው ላይ “ለሕፃናት ቦታ የለንም” የሚል ማስታወሻ ይጨመርበታል። የዶኪማስ ሰርግ ግን እናት ከልጅ፣ መምህር ከደቀ መዝሙር ተነጣጥለው የሚለዩበት አልነበረም። ምክንያቱም እናት ከልጅ አትነጠልም፤ ልጅም ከእናት አይነጠልም። መምህር ከደቀ መዝሙር ደቀ መዝሙርም ከመምህር አይነጠሉም።

በቅዱስ ወንጌል (ዮሐ.፪፥፩) ላይ የተጻፈውንና ከላይም የተጠቀሰውን ፅንሰ ሐሳብ መተርጒማኑ ሲያብራሩ “እናትን ጠርቶ ልጅን መተው ፈሊጥ አይደለምና እናታችን ቅድስት ማርያም ስትጠራ ልጇም ተጠራ። መምህርን ጠርቶ ደቀ መዝሙርን መተው አግባብ አይደለምና ጌታችን ሲጠራ ደቀ መዛሙርቱም አብረው ተጠሩ” ብለው አብራርተውታል። በመሆኑም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አክብሮ ወደጠራው ባለ ሰርግ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሄደ።

መምህር የሚደምቀው በደቀ መዛሙርቱ ነው። ደቀ መዛሙርትም የሚከበሩት በመምህራቸው ነው። ምንም እንኳን ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ድምቀት ሆኑት ባንልም ግን በቅዱስ ወንጌል “ያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል፤ ይገድሏችኋልም፤ ስለ ስሜም በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ” (ማቴ.፳፬፥፱) እንደተባሉ ስሙን ለአሕዛብ አሳውቀዋል፤ በስሙ መከራ ተቀብለዋል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት “ስለ እርሱ ሁልጊዜ ይገድሉናል፤ እንደሚታረዱ በጎችም ኾነናል” (መዝ.፵፫፥፳፪) በማለት እንደተናገረው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ለሮሜ ምእመናን በላከው መልእክቱ “ስለ አንተ ዘወትር ይገድሉናል፤ እንደሚታረዱ በጎችም ኾነናል፤ ነገር ግን በወደደን በእርሱ ሁሉን ድል እንነሣለን” (ሮሜ.፰፥፴፮)

በማለት እንደገለጸው በስሙ መከራን ተቀብለው፣ መከራ ተቀብለው ብቻ ሳይቀሩ በስሙ አጋንንትን አውጥተው፤ በስሙን ሕሙማንን ፈውሰው፤ በስሙ ሙታንን አስነሥተው፤ በስሙ የዚህን ዓለም መከራ ድል አድርገው አምላክነቱን ላላወቁት አሳውቀዋልና በእነርሱ የታወቀ ሆኗል። እነርሱም በእርሱ ከብረዋል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰርግ ቤት ሲሄድ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ ሄደ ሁሉ ዛሬም በመምህራን ላይ አድሮ ይኖራልና ካህናቱን መምህራኑን፣ በእግዚአብሔር ስም የተላኩትን ሁሉ ስንጠራ ጌታችንም እንደማይለይ ያስረዳናል። ምእመናን ካህናቱን ወደ ሰርግ ቤት ሲጠሩ መምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ አብሯቸው እንደሚጠራ መረዳት ይኖርባቸዋል። በቅዱስ ወንጌልም "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል" (ማቴ.፲፥፵) ተብሎ ተጽፏል።

**ለምን ተጠሩ፡-** ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራው ለሰርግ ነው። ሊቃውንቱ ተባብረው እንደገለጹት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ " ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፤ ከኃጢአት ብቻ በቀር እንደኛ ሰው ሆነ" (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ) ተብሎ እንደተነገረ በተዋሐደው ሥጋ ወደ ሰርግ ቤት ተጠራ። እርሱም በሰርጉ ቤት በመገኘት ጋብቻቸውን ይባርክ ዘንድ ጥሪውን አክብሮ ከደቀ መዛሙርቱና ከእናቱ ጋር ሄደ።

ጌታችን መድኃኒታችን ለሰርግ ሲጠራ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ሄደ። ይህም በማኅበራዊ ሕይወት እርሱ እንደተሳተፈ ደቀ መዛሙርቱም መሳተፍ እንዳለባቸው ሲያስረዳ ነው። ይህ ብቻም ሳይሆን በዚህ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ለባለ ሰርጉ ያደረገው ተአምር፣ ዛሬም በእርሱ እግር የተተኩትና ለክርስቶስ እንደራሴ ሆነው ምእመናንን ከክርስቶስ የሚያገናኙ መምህራን በሰርግ ቤትም ተገኝተው ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ማከናወን እንዳለባቸው ያስረዳል።

## ከዚህ ምን እንማራለን

**አንዱን ከሌላው ሳይነጣጥሉ መጥራትን፡-** ከላይም እንደተገለጸው ባለ ሰርጉ መምህሩን ሲጠራ ደቀ መዛሙርቱን፣ እና እናቱን አብሮ ጠራ። ዛሬም በኀዘን በደስታችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጠርተን እናቱን ድንግል ማርያምንና እርሱ ያከበራቸው ቅዱሳንን መጥራት እዳለብን ያስተምረናል። እንዲሁ ሰርጋችንን አዘጋጅተን መምህራንን ስንጠራ ደቀ መዛሙርቱንም መጥራት እንዳለብን፣ እናት አባትን ጠርተን ልጆችንም መጥራት እንዳለብንም ያስተምረናል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብዣ እንኳን አዘጋጅተን ሰዎችን ስንጠራ ማንን መጥራት ማንን ደግሞ መጥራት እንደሌለብን ሲያስተምር እንዲህ በማለት ተናግሯል። "በበዓል ምሳ ወይም ራት በምታደርግበት ጊዜ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን፣ ዘመዶችህንና ጎረቤቶችህን፣ ባለጸጎች ባልንጀሮችህንም አትጥራ፤ እነርሱም ይጠሩሃልና፤ ብድርም ይሆንብሃልና። ነገር ግን በበዓል ምሳ በምታደርግበት ጊዜ ድሆችንና ጦም አዳሪዎችን፤ ዕውሮችን፣ እጅና እግርም የሌላቸውን ጥራ። አንተም ብፁዕ ትሆናለህ የሚከፍሉህ የላቸውምና፤ ነገር ግን ጻድቃን በሚነሡበት ጊዜ ዋጋህን ታገኛለህ" (ሉቃ.፲፬፥፲፪-፲፬) እንዲል። ይህ ቃል የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምሳ ግብዣ ከተጠሩት አንዱን ሰው በዚህ መልኩ አስተምሮታል። ለጊዜው ለሰውየው የተሰጠው ይህ ትምህርት ሰዎች እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ሲማሩበት ይኖራል።

**ተጠርቶ አለመቅረትን፡-** ጌታችን መድኃኒታችን አስወድዶ አስፈቅዶ የሚገዛ አምላክ ነው። ስለዚህ ለድኅነታችን ሁሉ እኛ ፈቃደኛ ሁነን በፍጹም እምነት ልንጠራው ይገባል። ሲጠሩም ጥሪን አክብሮ መሄድ እንዳለብን እንማራለን። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠርቶ አልቀረም። ዛሬም ድሀም ይጥራን ሀብታምም ይጥራን "ሳትጠራ አትሂድ፤ ተጠርተህም አትቅር" እንዲሉ አበው ጥሪን አክብሮ መሄድ እንዳለብን ያስረዳናል።

በመጽሐፈ ሲራክ "ለባለጸጋውና ለከበርቴው ለድሃውም ክብራቸው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ድሃውን ስለ ድህነቱ ይንቁት ዘንድ አይገባም፤ ኃጢአተኛውንም ሰው ስለ ባለጸግነቱ ያከብሩት ዘንድ አይገባም" (ሲራ.፲፥፳፪-፳፫) ተብሎ እንደ ተጻፈ ማንም ሰው የደስታዬ ተካፋይ ሁኑልኝ ብሎ ሲጠራን ድሃና ሀብታም ሳንለይ ጥሪውን አክብረን መሄድ ይኖርብናል። ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የምንማረውም ይህን ነው። ምክንያቱም ማኅበራዊ ሕይወትን

ሊባርክ በድሃ ቤትም በሀብታም ቤትም፣ በሰርግም በኀዘንም ተገኝቶ መስተናገድ ባለበት አግባብ ተስተናግዷል።

**የባለ ጉዳዩን ችግር መረዳትን፡-** እኛን የጠራ አካል አስቦና አክብሮ ሲጠራን በወቅቱ የሚኖረውን ችግር መረዳት ያስፈልጋል። በክብር ተጠርተው ከሄዱ በኋላ በሆነ ባልሆነው የሚያኮርፉ፣ መስተንግዶው ሳያልቅ አቋርጠው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ሰዎች ይስተዋላሉ። በአስተናጋጆች ላይ የሚቆጡ፤ ቦታ አልተመቸኝም የሚሉ፣ ቅድሚያ አልተሰጠኝም ወዘተ የሚሉ አሉ። ነገር ግን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ካደረገው ተአምር የምንረዳው አስቀድሞ የጠሪውን ጉድለት ማወቅና ለመሙላት ፈቃደኛ መሆን የምንችለውንም ሁሉ ማድረግ እንዳለበን ነው።

በመጽሐፈ ሲራክ "በደስታህ ጊዜ አትታጣ፤ በኅ ድርሻህም አያምልጥህ" (ሲራ.፲፬፥፲፬) ተብሎ እንደተጻፈ ከላይም እንደተገለጸው አስቀድሞ ጥሪን አክብሮ መገኘት ከተገኙ በኋላም የድርሻን መወጣት ያስፈልጋል። ማለትም ከደስታው መካፈል በተጠራንበት ወቅት የሚጎድል ነገር ቢኖር ደግሞ የጎደለውን ነገር በአግባቡ ተረድቶ ለመሙላት መዘጋጀት ያስፈልጋል።

**ችግሩን መሙላትን፡-** ጌታችንና መድኃኒታችን ሁሉ ይቻለዋልና የባለ ሰርጉን ጉድለት ሞላለት። እንደ ሰው ወደ ሰርግ ቤት ተጠርቶ መብላቱ፣ መጠጣቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ደግሞ በተገኘበት ቤት የጎደለውን መሙላት መቻል ደግሞ እጅግ የሚደንቅ ነው። ዛሬ እኛ ምንም እንኳን " ለሚያምን ሁሉ ይቻላል" (ማር.፱፥፳፫) ተብሎ በቅዱስ ወንጌል ቢነገርም ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ ላይቻለን ይችላል። ምክንያቱም ተአምር እንደ እምነታችን መጠንና እንደተሰጠን ጸጋ መጠን ስለሆነ ነው። ነገር ግን ቢያንስ አስቀድመን ችግሩን መረዳት፣ ከዚያም የምንችለውን ሁሉ ማድረግ የክርስቶስን ፈለግ መከተል ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአግባቡ የጠራውን ሰው የሚያስተናግድ እህልና ውኃ ሳይኖርህ ለምን ጠራህ ብሎ ጥሎት አልሄደም። በእርግጥ ይህ ሰዓት ለባለሰርጉም ለአሳላፊዎችም እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያሸብር ሰዓት ነበር። ግን ጭንቀታቸውን የተረዳች ድንግል ማርያም ወደ ልጇ አመለከተች፤ የሁሉን ችግር የሚሞላ፣ ሁሉን የሚያደርግ አምላክም የሰዎችን ችግር ተደርቶ የጎደለውን ሞላላቸው።

በአጠቃላይ "በገሊላ ክፍል በቃና ሰርግ ኾነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰርግ ቤት ተጠራ፤ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሄደ" በማለት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የገለጸው በቅዱስ ወንጌልም የተጻፈው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም በመጣበት ወራት በቃል ያስተማረው፣ በተግባር የፈጸመው እኛም በሕይወታችን እንድንኖረው የሠራልን ሥርዓት ነው። በማኅበራዊ ሕይወታችን እንድንገለገልበት ከሠራልን ሥርዐት ባለፈ ነገረ ድኅነትን የምንረዳበት ትምህርቱም ነው።

ስለዚህ ባለ ሰርጉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከእናቱ ጋር እንደጠራ እርሱም ጥሪውን አክብሮ ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ሰርግ ቤት እንደሄደ ሁሉ እኛም በኀዘን በደስታችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱ ክርስቶስን ስንጠራ እናቱና ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ያከበራቸው ቅዱሳንም የማይቀሩ መሆናቸውን፣ በማኅበራዊ ሕይወታችን መምህርን ከደቀ መዝሙር እናትን ከልጅ እየለዩ መጥራት አግባብ እንዳልሆነ እንማርበታለን። ጌታችን ከእናቱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመጠራቱና በመሄዱ የሰርጉን ቤት ጉደሎ እንደሞላ ሁሉ የእኛንም ዝግጅት የሚያከናውነው "እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ" (ማቴ.፲፥፵) በማለት በቅዱስ ወንጌል እንደተናገረው መምህራንን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መጥራት እንዳለብን ያስረዳናል። በዚህም የጎደለንን ሁሉ እንደሚሞላልን ልናምን ይገባናል። በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ የጎደለውን የሞላ አምላካችን በእኛም ሕይወት ሁል ጊዜ እየተገኘ የጎደለንን እንዲሞላልን የእርሱ አባታዊ ቸርነት፣ የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳኑ ተራዳኢነት አይለየን አሜን።

✝ ✝ ✝

# ታሪኩ

## ኪነ ጥበብ

*በመዝሙርና ሥነ ጥበባት አገልግሎት ማስተባበሪ*

ሥራዬን አልወደውም፡፡ ፈጣሪ ሆን ብሎ የፈረደብኝ ይመስለኛል፡፡ ሥራዬን ብተወው ደግሞ እቸገራለሁ፤ ይርበኛል፡፡ እንዳልተወው ችግሩ እያስጨነቀኝ እንዳልቀጥል ደግሞ ጠልቼው ሁል ጊዜም እየተማረርኩ ወደ ሥራ ሄዳለሁ፡፡ እሠራለሁ እሠራለሁ.... ወገቤን ... ወይኔ ሲያደክም ደሞ... የሆነ ችክ ያለ ሥራ ነው፡፡ እዚያ አንገቴን ደፍቼ ስቆፍር ስቆፍር እውልና... ፊቴን አጨፍግጌ ሲመሽ ወደ ቤቴ እያዘገምሁ እሄዳለሁ፡፡ መንገድ ላይ ሰው አያወራኝም፡፡ ልብሴ አቧራ ስለሆነ ይሁን... ፊቴ ስለተከሰከሰ... እኔ እንጃ ብቻ... ለነገሩ እኔም ቢያወሩኝ የምመልስላቸው አይመስለኝም፡፡ ደህናና ረዘም ያለ ወሬ ካወራሁ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል ፡፡

ወደ ቤቴ ስሔድ እግሬ ለምዶበት ራት ወደምበላበት ቤት ይወስደኛል ገብቼ እንደተቀመጥሁ ከአፍታ በኋላ የተለመደችው ልጅ የተለመደውን ምግብ ታመጣልኛለች፡፡ የምበላውን ስለምታውቅ ሳልነግራት ነው የምታመጣልኝ... ለትዕዛዝ እንኳን አላወራም፡፡ እጄን በውኃ አርስና ቆረስ አድርጌ ወደ አፌ ሳስጠጋ ከንፈሬ ይላቀቃል... በቀስታ እበላለሁ፡፡ አላምጬ ስውጥ ራሱ ሔዶ ሆዴ ውስጥ ሲቀመጥ ድምፁ የሚሰማኝ ይመስለኛል፡፡

ትክ ብዬ አየዋለሁ የምበላውን ሽሮ ወጥ፡፡ በውስጤ እሰድበዋለሁ፡፡ በልቼ ስጨርስ መልስ እንዳይኖረው አድርጌ ከኪሴ ዝርዝር ፈልጌ ሒሳቡን ከፍዬ እወጣለሁ፡፡ መልስ ያለው ገንዘብ ስሰጥ ያወራሁ ይመስለኛል፡፡ የሆነ አለ አይደል... እየጠበቅሁሽ ነው መልሱን.... ዐይነት፡፡ በቃል ባናወራም ልቦቻችን አይኖቻችን ያወራሉ፡፡ እሱን ነገር አልፈልገውም፡፡ ዝርዝሩን አስቀምጬ እወጣለሁ ወደ ቤቴ፡፡ አንዳንድ ቀን ኪሴ ሲፈቅድልኝ ወደ አረቂ ቤት ጎራ ብየ የነደደውን ውስጤን እንደገና በአረቂ ቅጥልልልል... አረገውና "የታባህና!!" እላለሁ ለራሴ፡፡ ትንሽ ስደጋግም የተለመደው ጥያቄ ወደ አእምሮዬ ይመጣና ትንሽዬ የምጸት ፈገግታ ፈገግ እላለሁ... "ምን ቢያስብ ነው አያቴ ታሪኩ ብሎ ስም ያወጣልኝ???"ይላል መደበኛው ጥያቄ፡፡

አባቴ የት ሄዶ እንደሆነ አላውቅም አያቴ ጋር ነው ያደግሁት፡፡ "ምንም የረባ ታሪክ ለሌለው ሰው ታሪኩ ብሎ ስም ማውጣት እንዴት ሞኝነት ነው..." እልና አረቄዬን ወደ ጉሮሮየ ወርወር አድርጌ የተለመደውን ዝርዝር አስቀምጬ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ፡፡ ቤቴ የቀበሌ ቤት ነው፡፡ ከሱሪዬ ጋር ታስሮ ተንጠልጥሎ የሚውለውን ቁልፍ ዳበስ አድርጌ አፈልግና በሩን ከፍቼ ወደ ቤቴ ገብቼ ጋደም ብየ ማሰብ እጀምራለሁ፡፡ ከፈጣሪ ጋር እከራከራለሁ... "ካልጠፋ ሥራ እንዴት መቃብር ቆፋሪ ታረገኛለህ?? ወይ አያዝናና ወይ ደህና ገንዘብ የለው... ምን አስበህ ነው??" እዚህኛው ሐሳብ ላይ ወይ ደግሞ ሌላ ሐሳብ ላይ እንቅልፍ ይዞኝ ይሄዳል፡፡ አንዳንዴ ፈጣሪ ከሰው ሁሉ ለይቶ "ታሪኩ ና ወዲህ... ላንተ የሚሆን ሁነኛ ሥራ አለኝ... እንደምታውቀው ሰው ማለት ሰብል ነው፡፡ መኸር ነው፡፡ ምርቱ ሲሰበሰብ እኔ ፍሬ ፍሬውን ወደኔ ሳመጣ አንተ ገለባውን እየሰበሰብህ ወደ ገደል ክተት፡፡ በል ሂድ፡፡" ያለኝ ይመስለኛል፡፡ የትም ሲባክን የነበረ ሰው ሁላ ማረፊያው የኔ መዳፍ ነው፡፡ ከባለ ሥልጣን እስከ የኔ ቢጤ፡፡ ከሀብታም እስከ ደሀ ሁሉንም እኩል እየተቀበልሁ አስተናግዳለሁ፡፡ እኔ ጋ ይመጣሉ አለቀ ከዚያ በኋላ የትም አይሄዱም፡፡ በዚህ ምክንያት መልአከ ሞት ራሱ "ታሪኩ እንደምን አደርህ አንተ ትልቅ ሰው፡፡" ሳይለኝ የሚውል አይመስለኝም፡፡ ፈጣሪ ነፍስን ወደ ሲኦልና ወደገነት ይሰበስባል፡፡ እኔ ሥጋቸውን ወደ መቃብር እሰበስባለሁ፡፡ በእንዲህ ዐይነት ሥራ እየሠራን መቼም አያየኝም አልልም፡፡ እንደዚህ ስሠቃይ...

በጣም የምጠላው ነገር ጥሩምባ ነው:: የእድር ጥሩምባ ለኔ በምድር ላይ ካሉ አሠቃቂ እና አናዳጅ ነገሮች አንደኛው ነው:: ካልጠፋ ጊዜ በሐሳብ ስባዝን አምሽቼ ጥሩ እንቅልፍ በምተኛበት የንጋት ሰዓት … ካልጠፋ እቃ ሰቅጣጭ ድምፅ ያለውን ጥሩምባ መርጠው ማጮህ ምን የሚሉት ምቀኝነት ነው?? ይሄ ጥሩምባ ተነፋ ማለት ለኔ “ታሪኩ ሆይ ከጣፋጭ እንቅልፍህ ተነሣና ወደማትወደው ሥራህ ሂድ…” የሚሉት የንጋት መርዶ ነው::

እነሣና እሄዳለሁ:: የሆነ ሰው ሞቷል:: ጃኬቴን ደርቤ ባርኔጣየን አድርጌ እጄን በኪሴ እከትና አቀርቅሬ ወደ ፊት ሳላይ እሄዳለሁ:: ዐይኔን ብታሰር እንኳን እግሮቼ ራሳቸው በዘልማድ ቀጥ አድርገው ይወስዱኛል ወደዚያ የመቃብር ስፍራ::

ስደርስ ቀሳውስት ተሰብስበው ዕጣን እያሻተቱ ፍትሐት እየፈቱ የሞተው ሰው ቤተ ሰቦች ጥቁርና ነጭ ደበላልቀው ለብሰው ከበው እያለቀሱ(አንዳንዴ ደክመው ሰው የደገፋቸውም ይመጣሉ) ይታያሉ:: እስኪጨርሱ አካፋየን ተደግፌ አያቸዋለሁ:: አያስቁኝም አያሳዝኑኝም:: ጥቂት ስለ ሬሳው እና ስለ አልቃሾቹ አስባለሁ:: ሰዓቱ ሲደርስ ሬሳውን አስቀድሞ አስተካክየ በቆፈርኩት ጉድጓድ ቀስ አድርገን እንከተውና ተጋግዘን ከየት መጣ ባልተባለ ፍጥነት አፈር እናለብሰዋለን:: ምንድነው ግን እዚህ ጋር ስንደርስ እንደዚህ የሚያስቸኩለን? የሟች ቤተሰቦች እንዳይሳቀቁ ነው? እኔ ራሴ በራሴ እገረማለሁ … ከየት እንደማመጣው ሞራል እና ፍጥነቴን:: ቀኑን ሙሉ ስለፋበት የዋልኩትን አፈር በደቂቃ መልሰን ደፍነነው እርፍ::

የሚቀበሩት ሰዎች ላይ ትንሽ በሐሳብ መጫዎት ልማዴ ነው:: አንዳንድ ሬሳዎች ወፍራም እና በብዙ አልቃሽ ታጅበው የሚመጡ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች በሕይወት እያሉ ወይ የተመቻቸው ናቸው:: ባለሥልጣን ምናምን ነገር… አንዳንድ ሬሳዎች ደግሞ ጸጥ ረጭ ያሉ ናቸው:: ብዙ አልቃሽ የላቸውም:: የመጡትም ብዙ አያለቅሱም:: አፈር ሳለብሳቸው አብሬ ካልተቀበርሁ ብሎ የሚያስቸግረኝ ሰው የላቸውም:: እንደኔ ምድብ እነዚህ ሰዎች ሰላማዊ ሰዎች ይባላሉ:: አካላቸውም ቀላል ነው:: አይረብሹም:: በጸጥታ ነው የኖሩት እዚህም ሲቀበሩ በጸጥታ ነው:: ለዚህ ነው ሰላማዊ የምላቸው:: ሌሎቹ ተቀብረውም አያርፉም:: በየቀኑ ስመጣ ሳያቸው መቃብራቸው ላይ ሻማ አበባ ምናምን…ብዙ ጩኸት ሰብስበው ነው ማገኛቸው:: ይህ ለኔ ጩኸት ነው:: እየኖሩም ቅራቅምቦ ያበዙ ነበር ተቀብረውም ያው ናቸው::

በየቀኑ እዚህ መቃብር ስፍራ ላይ ነኝ:: ሌላ ቦታ አልሄድም:: ሰው የማይሞትበት ቀን የለም:: ከብዙ ዓመታት በኋላ ቆይ……ቶ ቆይቶ የሆነ ቀን አመመኝና አልጋዬ ላይ ተኝቼ በጸጥታ አስባለሁ:: እይታዬ እንደ መደብዘዝ አስተሳስቤ እንደ መደንዘዝ እያለ መጣ:: ቤቴ ሰው ገብቶ አያውቅም ነበር:: ትንሽ ዐይኔን ገርበብ አድርጌ ሳይ ቤቴ ውስጥ ሰው ያየሁ መሰለኝ:: በየመሃሉ የሆነ ጥራት የሌለው የማይሰማ ወሬ የምሰማ ይመስለኛል:: ተመልሶ ጸጥ ይላል:: ትንፋሽ እያጠረኝ መጣ:: “ምን ሆኘ ነው ልሞት ነው እንዴ?” አልኩ ለሐሳቤ:: አዎ ነው ማለት ነው:: አልቀረልኝም ሞት ወሰደኝ:: ሌላ ዓለም ውስጥ የገባሁ መሰለኝ:: ሰዎች ተሰበሰቡ ግን አያለቅሱም:: እሰይ እንኳንም አያለቅሱ:: ሰላማዊ ሟች ነው መሆን የምፈልገው:: ሰውነቴን ገነዙኝ እና በእድሩ የሬሳ አልጋ አድርገው ተሸክመው ሲወስዱኝ በጣም ደነገጥሁ:: አሁንም ሞቼም ወደ ሥራ ቦታ ልሄድ ነው?? በሕይወት እያለሁም የማልወደው የሚያማርረኝ ሥራዬ አሁንም ሞቼ ልሄድበት ነው? ምን ዓይነት አለመታደል ነው ይሄ?? ማን ቢረግመኝ ነው እንደዚህ ከሞትም በኋላ የምማረረው?? “አውርዱኝ ወደ ሥራ ቦታ መሄድ አልፈልግም! እቤቴ ውስጥ ቅበሩኝ የሥራ ቦታዬን አልወደውም!” ብየ መጮህ ፈለግሁ:: አልቻልኩም:: ይዘውኝ ሄዱ ድሮ በእግሬ በምሄድባት መንገድ:: ደግሞ ፍጥነታቸው:: ምንድነው የሚያጣድፋቸው?? አናደዱኝ:: ቢያንስ ቀስ ብለው አይወስዱኝም??

የመቃብር ቦታው ስንደርስ አውርደው ገጭ አደረጉኝ:: “ኧረ ቀስ! እንዴ ገና ለገና ሞቷል ተብሎ ወገቤን ሊሰብሩት ነው እንዴ?” ቄሶቹ ጸሎተ ፍትሐት ጀመሩ:: በሕይወት እያለሁ ለሌላ ሰው ሲያደርሱ አካፋዬን ተደግፌ እንደማዳምጣቸው አሁንም ዝም ብየ አዳመጥኳቸው:: ሲጨርሱ ከአልጋው አንሥተው የተቆፈረው መቃብር ውስጥ አስተኙኝ:: ምን ዓይነት ቀሽም መቃብር ቆፋሪ ነው የቆፈረው ባክህ…. አይመችም ወጣ ገባ አድርጎ ነው የቆፈረው:: ኤጭ!… ዶማ ዝም ብሎ እጅ እንዳመጣ ይጣላል እንዴ? አቆፋፈርም እኮ

ጥበብ አለው፡፡ መቃብር መቆፈር እኮ ኪን ነው፡፡ ዝም ብሎ መሬት ስለሆነ ብቻ በመቆፈሪያ አይደለዝም… ስንት ዓይነት ሰው አለ በናታችሁ፡፡ ወይ ምናለበት የራሴን መቃብር እንድቆፍር ቢነግሩኝ ሳልሞት፡፡ እንዴት አላሰብኩትም? ለዚያ ሁሉ ሰው ፍራሽ የተነጠፈበት አስመስየ ስቆፍር ስደለድል እንዴት ለራሴ መቃብር ሳልቆፍር ቀረሁ? ወይኔ! “እሽ ቢያንስ አፈር ከስር ደልድሉልኝ ይህ ሰውዬ መቃብር ሳይሆን የቆፈረው ተራ ገደል ነው፡፡” ማለት አማረኝ ግን እንዴት..፡፡ ግድ የላቸውም፡፡ አፈር አለበሱኝና ፊታቸውን አዙረው ሄዱ፡፡ ወይኔ ሲቆረቁር…፡፡

ነፍሴን መልአከ ሞት ይዞ ወደ ሰማይ እየወጣ እያለ አየሁት… አየኝ… ከፍ እያልን ስንሄድ ብርሃኑ እየተለወጠ የማላውቀው ዓይነት ብርሃን ውስጥ ገባን፡፡ ትንሽ ፍርሀት እየተሰማኝ መጣ፡፡ መልአከ ሞት ለአንድ ሌላ መልአክ አቀበለኝና ያ መልአክ በስተምዕራብ በኩል ይዞኝ ወደ ሲኦል ነጎደ፡፡ ፈራሁ ጨኸቱ እየበረታ ሰቅጣጭ ድምፁ እየጎላ መጣ፡፡ “ወደየት ነው የምትወስደኝ?” አልኩት፡፡ ጥቂት ዝም ብሎኝ ቆየና… የሆነ ከዚህ በፊት ሰምቸው በማላውቀው ድምፅ “ ዝቅ ብለህ ተመልከት፡፡ ይህ ሲኦል ይባላል፡፡ ለሰባት ቀን ይህንን ትጎበኛለህ፡፡ ይህ በምድር እያሉ ፈጣሪያቸውን አምላካቸውን የረሱ …ኃጢአት ሲሠሩ ሰው ሲበድሉ የነበሩ ነፍሶች መኖሪያ ነው፡፡ አለቃቸው ዲያብሎስ ነው እንደወደደ ያደርጋቸዋል፡፡..” በምን ቋንቋ እንደሚያወራ ባላውቅም ግን ይገባኛል… በልጅነቴ አአትሪኮን፣ ቦርፎሪኮን፣ እና አተርጋዎን የሚባሉ ቋንቋዎች እንዳሉና ከነዚህ ውስጥ የትኛው እንደሆነ ባላስታውስም አንደኛው የመላእክት ቋንቋ እንደሆነ በልጅነቴ የተማርኩት ትዝ አለኝ፡፡ እንዴት ረሳሁት…፡፡

የሲኦልን አስፈሪነት ሳይ ልቤ ወከክ አለ፡፡ ብዙ ነፍሶች ገብረተው እየተቃጠሉ ይጮሀሉ፡፡ አጋንንት በላይ በላይ ስቃዩን ያጸኑባቸዋል፡፡ ይጨክኑባቸዋል፡፡ እንባዬ እየፈሰሰ ነበር…፡፡ ነፍሴ እየተንቀጠቀጠች ነው፡፡ ለሰባት ቀናት አስከፊ የሚባሉትን የሲኦል ጉራንጉር ሁሉ የጭካኔን ጥግ አየሁ፡፡ ነፍሴ ለሳምንት ተሸማቅቃ ሰነበተች፡፡ እውነት ለመናገር ሰባቱ ቀናት እንደ ሰባት መቶ ዓመታት ነው የረዘሙብኝ፡፡ መልአኩ በሰባተኛው ቀን መጨረሻ “በምድር ክፉ ሠርተህ ከሆነ ቀሪውን ዘመን እስከ ዕለተ ምጽአት እዚህ ትቆይና ከዕለተ ምጽአት በኋላ ወደ ባሰው ሥቃይ ወደ ገሀነም ትሄዳለህ፡፡ በዚያ ለዘለዓለም ትኖራለህ፡፡ ዓለምም ታልፋለች፡፡” አለኝ፡፡ እኔ ምንም አልመልስለትም በፍርሃት ብቻ አየዋለሁ፡፡

ወዲያው ወደ ምሥራቅ ይዞኝ ሄደ፡፡ እጅግ የሚያምር ቦታ ነው፡፡ ገነት ነው አልኩ በውስጤ፡፡ ብዙ ነፍሶች አሉ፡፡ ነጫጭ ናቸው፡፡ ጸዓዳ፡፡ የሚያስጎበኘኝ መልአክ በሚያወራበት ልሳን ነው ሚያወሩት፡፡ ሁሉም አንድ ዓይነት ነገር በአንድነት ይላሉ፡፡ “ቅዳሴ ነው?” አልኩት መልአኩን ቀና ብዬ፡፡ “ይህ ገነት ነው፡፡ በምድር ሳሉ መልካም ነገርን የሚያዘወትሩ ደጋግ ነፍሶች መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው እና ፈጣሪ በምሕረት የጎበኛቸው ናቸው፡፡ ለሰባት ቀናት በዚህ ትቆያለህ፡፡ በምድር ደግ ነገርን የሠራህ ቢሆን ወይም ፈጣሪ በምሕረት ቢጎበኝህ በዚህ ትኖራለህ፡፡…” እያለ ይዘረዝርልኝ ጀመር፡፡ እኔ በሁኔታው ተደንቄ አፌን ከፍቼ ወደ ገነት እያየሁ ተገርሜ ቀረሁ፡፡ ነፍሴ መለምለም ጀመረች፡፡ በጣም ደስታ ተሰማኝ፡፡ እንዴት እንደሆነ ሳላውቀው ሰባተኛው ቀን አለቀና መልአኩ መልሶ ይዞኝ ሔደ፡፡

አሁን ደግሞ ወደ የት ይዞኝ ሊሄድ ነው ስል “ አሥራ አራት ቀናትን ሁሉንም እያየህ ቆይተሀል፡፡ አሁን ፍርድን ወደሚሰጠው ፈጣሪህ ፊት ቆመህ ፍርድህን ትቀበላለህ፡፡” አለኝ፡፡ ወደየት እወድቅ ይሆን ብየ ደነገጥሁ፡፡

እጅግ ያማረ አይቼው የማላውቀው ብርሃን ውስጥ ይዞኝ ገባ፡፡ ነፍሴ ከፍርሀት የተነሣ መቆም አልቻለችም፡፡ ጥቂት ቆይቶ አንድ ሌላ መልአክ ሚዛን ይዞ ቀረበና ጽድቅና ኩነኔዬን በግራና በቀኝ አድርጎ አስቀመጣቸው፡፡ በግራ በኩል ከመጠን በላይ አጋደለ፡፡ ኩነኔዬ መብዛቱ ነበር፡፡ ሌላው መልአክ ቆሞ አንድ ተለቅ ያለ መጽሐፍ ይዞ ያነብ ጀመር፡፡ ይሄኛው ጠንቅቆ የሚያውቀኝ ይመስለኛል፡፡ እያንዳንዷን ሥራዬን ነው እየዘረዘረ የሚያነባት፡፡ ጠባቂ መልአክ የሚባለው ይህ ነው እንዴ? “በቃ አለቀልኝ የሲኦል ራት ሆንኩ” ብየ ተስፋ ቆረጥሁ፡፡ ጥቂት ቆይቶ “ታሪኩ ልጄ እኔ አምላክህ ነኝ፡፡ ሕይወትህን ሙሉ በዝምታ እና በቸልተኝነት ጨረስካት፡፡ በየቀኑ በተግባር የሚመክር ሞትን ፊት ለፊት የሚያይ እንዳንተ ማን ነበር… ነገር ግን ለመሞት አልተዘጋጀህም ነበር … ሞትህን ዐውቀህ

ተዘጋጅተህ አታውቅም፡፡ በዕድሜ ካንተ የሚያንሰውን.. በዕድሜ ካንተ የሚበልጠውን … በሀብት ካንተ የተሻለውን …ካንተም የደኸየውን ሞት ወዳንተ ሲያመጣው… ስለምን ልብህ አልደነገጠም? ግብአተ መሬትህን ሲፈጽሙ በስብሶ ስለሚቀር ስለ ሥጋህ ዕረፍት እንጂ ስለ ነፍስህ መውደቂያ ለምን ማሰብ አልቻልክም? አሁንም ቤትህን አስተካክለህ ለዘለዓለም ሕይወት እንድትበቃ በጎ ሥራንም እንድትሠራ ስለምሻ መላእክት ነፍስህን ከሥጋህ መልሰው ያዋሕዳሉ፡፡ ሕይወትህ ባይታደስ ለጽድቅም ባትበቃ እጣ ፋንታህ ሲኦል ይሆናል፡፡" ብሎኝ ሲጨርስ ያ የሚጣፍጥ ድምፅ ከጎኔ የነበረው መልአክ መለከቱን ጆሮዬ ላይ ነፋው፡፡

ድምፁ አስበርግጎኝ ብንን ብየ ነቃሁ፡፡ ቤቴ ውስጥ አልጋዬ ላይ ነኝ፡፡ ቀስ ብየ አማተብኩ፡፡ የቅድሙ መለከት ሚመስለው ድምፅ መልሶ ተነፋ፡፡ የእድሩ ጥሩምባ ነበር፡፡ ዙሪያዬን ቃኘሁ በመስኮቱ እና በበሩ የገባው ደብዛዛ የብርሃን ጭላንጭል ወገግ እያለ እንደሆነ ያስታውቃል፡፡

በሕልሜ ነው ወይስ እውነት ሞቼ ነበር?? ከሞትኩ….. ተቀብሬ ነበር…እንዴት አልጋዬ ላይ ሆንኩ አሁን?? እንደዚህ ዓይነት ሕልም አለ እንዴ?? አእምሮዬ በጥያቄ ተወጠረ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ጥሩምባው ከቤቴ አጠገብ መጥቶ ጮኸ፡፡ ደንገጥ ብዬ ተነሣሁና ጫማዬን ለብሼ ልብሴን እንደነገሩ አድርጌ፡፡ ወደ መቃብር ስፍራው በጥድፊያ ሄድኩ፡፡ እርምጃዬ ከወትሮው የተለየበት የመንገዱ ዳር ባለ ሱቅ አንገቱን ወጣ አድርጎ ከዓይኑ እስክሰወር ያየኛል፡፡ ሐሳቤ በሙሉ መቃብር ቦታው ላይ ነው፡፡ እግሬ ስለለመደበት ነው ዝም ብሎ የሚወስደኝ እንጂ መንገዴን አላስተውልም፡፡

ደረስኩ፡፡ ትናንት የቆፈርኩትን መቃብር ሄድኩና አየሁት፡፡ የለቅሶ ድምፅ ሰማሁ፡፡ ሬሳ በአልጋ ተይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ገባ፡፡ ኪዳን እየተደረሰ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ አዞሩት እና በወንዶች መግቢያ በር ፊት ለፊት አስቀመጡት፡፡ ቀስ እያልኩ ሬሳውን ብቻ እያየሁ ተጠጋሁት፡፡ ወደ አንድ ጥግ አንሥተው ወሰዱና ጸሎተ ፍትሐት ተጀመረ፡፡ ሐሳቤ ከሕልሜ ሳይላቀቅ ፍትሐቱ እስኪያልቅ ደንዝዤ ቆምኩ፡፡ ስለ ሟች አሰብኩ አሰብኩ… ድንገት አስከሬኑን አንሥተው አራት ሰዎች ሲሸከሙት ከሐሳቤ ገታ አልኩና ወደሚሄዱበት ተከተልኳቸው፡፡ ወደ መቃብሩ ሲደርሱ ከፊት ቀደም ብዬ የቆፈርኩትን መቃብር በሕልሜ እኔን እንደቆረቆረኝ እንዳይቆረቁረው አስተካከልኩለት፡፡ ቀስ አድርገን አስተኛንና አፈር አለበስነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙት አዘንኩ፡፡ እንባዬ ሊመጣ ፈለገ፡፡ አገድሁት እና ዋጥሁት፡፡ መቃብር ቆፋሪ አያለቅስም!

ሰዎቹ ወዲያው ወደ መጡበት ተመለሱ፡፡ እኔና ሟቹ ብቻ ቀረን በቦታው፡፡ መጨረሻው እኔ ነኝ መጨረሻዬ እሱ ነው… አየሁት በትካዜ አተያይ፡፡ ከጎኑ በጎ ቦታ አየሁና ቀስስስ ብዬ ተነሣሁ፡፡ "ለምን ከመሞቴ በፊት የራሴን መቃብር እዚች ቦታ ላይ እንደምፈልገው አድርጌ ማልቆፍረው??" ራሴን አማከርኩት፡፡ ተስማማሁ፡፡ መቆፈሪያየን አስደግፌ ካስቀመጥኩበት ዛፍ ለማምጣት ስሔድ … አንድ ካህን ዛፉ ስር ቁጭ ብለው ዳዊት ይደግማሉ፡፡ ደነገጥኩና በቆምኩበት እርሳቸውን አሻግሬ ማየት ጀመርኩ፡፡ ቄሰ ገበዙ ናቸው፡፡ ያውቁኛል፡፡ ውስጤ በድጋሜ ተምታታ፡፡ በቀስታ እርምጃዬን የመቆጠብ ያክል ወደ ካህኑ መጠጋት ጀመርኩ፡፡ መቆፈሪያዬ ከጎናቸው ዛፉን ተደግፎ ይታየኛል፡፡

ቀስ ብየ ሳልረብሻቸው መቆፈሪያዬን ማምጣት ነው ያሰብኩት፡፡ ወደ ርሳቸው ለመድረስ ጥቂት እርምጃ ሲቀረኝ አንድ የደረቀ ቅጠል ተጠጋሁና ተንኮሻኮሸ፡፡ ባለሁበት ቆምኩ፡፡ "እንደምን አደርህ ታሪኩ…" አሉኝ ጥቂት ካስተዋሉኝ በኋላ፡፡ ወዲያው በሰማይ የሆነው ትዝ አለኝና… ከእግራቸው ስር ቁጭ ብዬ ብዙ ካሰብኩ በኋላ የሆነውን ሁሉ ነገርኳቸው፡፡ አዘኑልኝ… ንስሓ እንድገባ አደረጉኝ፡፡ ቀኖናዬን ተቀብዬ መቆፈሪያዬን አንሥቼ ነገ ሌላ ሰው መሞቱ ስለማይቀር በዝምታ አዲስ መቃብር ስቆፍር ውዬ ሲመሻሽ የራሴን መቃብር መቆፈሩን ለሌላ ቀን ብዬ ወደ ሰፈሬ መንገድ ጀመርኩ፡፡

አንደበቴ ከሰው መነጋገር ጀመረ፡፡ በሄድኩበት ሁሉ ከሰዎች ጋር አወራሁ፡፡ ራቴን በልቼ አረቄ ቤቱን አልፌ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ፈገግ ብዬ ነበር፡፡ ማታ ሕልም ካየሁባት አልጋ ላይ ጋደም አልኩ፡፡ እረፍት ተሰማኝ፡፡ ሰላማዊ እና ማጉረምረም የሌለበት እንቅልፍ ተኛሁ፡፡ የነገው ጥሩምባ ድምፅ አያነጫንጨኝም፡፡ ይልቁንም ነፍሴን ለንስሓ የሚቀሰቅስ የሚጎሽም መለከት ነው፡፡ አያቴ ልክ ነበር፡፡ ታሪኩ ብሎ ስም ያወጣልኝ፡፡

✞ ✞ ✞

# ''ሰላም እንዲሰፍን የቤተክርስቲያን ድርሻ''



*በዳዊት ደስታ*

## ሰላም ምንድን ነው?

ሰላም በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው። የሰው ልጆች በምንኖረው ሕይወት ውስጥ እጅጉን ከሚያስፈልገን ነገር ዋነኛው ሰላም ነው። ፍጥረታት እንዲኖሩ የሚያስፈልገው በሰላም ነው ያለ ሰላም ልንኖር አንችልም። ሰላም ማለት ‹‹ፍጹም፣ ጤና፣ ዕረፍት፣ ዕርቅ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደኅንነት፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሰላምታ፣ የቡራኬ የምርቃት ቃል፣ ሰው ሲገናኝ ሲለያይ የሚለው የሚናገረው ወይም የሚጽፈው›› በማለት  አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የሰላምን ፍቺ በእንዲህ መልኩ ገልጸውታል። (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፳፻፳፳)

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ‹‹የሰላም ግንባታ ማሠልጠኛ›› በተሰኘው ጥናታዊ መድበሉ ስለ ሰላም ምንነት እንደሚከተለው አብራርቷል። ‹‹ሰላም የሚለው የአማርኛ ቃል የተሸከመው ፅንሰ ሐሳብ ከጦርነትና ከዐመፅ ነፃ መሆን›› ከሚለው የአንዳንድ መዛግብት ቃላት ሰፋ ያለ ትርጉም ይዟል። ‹‹ሰላም›› ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታና ውድ ጸጋ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔር ሰላም ነው›› (መሳ. ፮፥፳፬) በማለት ማረጋገጫ ሰጥቶናል።

እውነተኛ ሰላም የሚገኘው የሰው ልጅ በክርስቶስ አምኖ፣ ከኀጢአቱ ነጽቶ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ ነው። ‹‹በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ››፤ ‹‹እርሱ ሰላማችን ነውና›› እንዲል። (ሮሜ ፭፥፩፤ ኤፌ. ፪፥፲፬-፲፯) ሰላም የመንፈስ ፍሬ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ከዘረዘራቸው መካከል የተጠቀሰ ነው። (ገላ. ፭፥፳፪) ‹‹ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ አንተንም ለሚወዱ ልማት ይሁን በኃይልህ ሰላም በጌጠኛ ቤትህም ልማት ይሁን›. እንዲል (መዝ. ፻፳፩፥፮-፯) በቅዱሳት መጻሕፍት ሰላም የሚለው መሠረታዊ ቃል የሚያመለክተው በሰዎች ሕይወት ውስጥ ተሟልቶ መገኘት የሚገባውን ደኅንነት፣ መላካምነት በመሆኑ ቃሉ የያዘው ፍቺ ላቅ ያለ አሳብን ነው። በሌላ አገላለጽ ሰላም ማለት ሰዎች በግል ኑሯቸውም ሆነ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ወቅት ሊኖራቸው የሚገባ ሁለንተናዊ ምሉእ የሆነ የሕይወት መገለጫ ነው።

የጸሎታችን ሁሉ ራስ በሆነው ጸሎተ ቅደሴያችን “ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ቀናች፣ የሐዋርያት ቅድስት ጉባኤ ስለ ሆነችው ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ” እያልን እንለምናለን።

## ቤተ ክርቲያን በሰላም ግንባታ ያላት ሚና

ከትላንት እስከ ዛሬ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በትንሹም በትልቁም የሰላም እና የዕርቅ ማዕከል ናት። በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተደረጉ የእርስ በእርስ ጦርነቶች የተለያዩ ዘሮች ጎሳዎች እና ስብስቦች የታረቁት እና የሚታረቁት በሃይማኖት አባቶች ነው። በሀገራት ደረጃም ከዲፕሎማሲው ጎን ለጎን የሃይማኖት አባቶች ሰላምን በማውረድ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። ባል ከሚስት ፣ ጎረቤት ከጎረቤት ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ አንድ ሰው ከሌላው በምክንያት ቢጣላ የዕርቀ ሰላሙን ሥራ የሚሠሩት የሃይማኖት አባቶች ናቸው። ‹‹የሚያስታርቁ ብጹዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና›› /ማቴ ፭፡ ፱/ የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያን ካህናት ሁል ጊዜ በሰላም ግንባታ እና በዕርቀ ሰላም ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዘው ኖረዋል፣ ዛሬም ወደ ፊትም ይህንን ተግባር የሚቀጥሉበት ነው።

በሀገራችን ትላንትም ሆነ ዛሬ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ጠብ እና ጦርነቶች ሲካሄዱ ኖረዋል ለምሳሌ ዘር እና ጎሳ ተኮር ጦርነቶች ከትላንት እስከ ዛሬ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ደም ሲያፋስ ነበር አሁንም እያገረሸ ሰው ከሰው እያለያየ ነው ለዚህ ፍቱን መድኃኒቱ መንግሥት ከሚወስደው የኃይል እርምጃ ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ምእመንዋን በማስተማር

ሊመጣ ካለው መዓት እና ጦርነት መታደግ እንደምትችል ብዙኃን ያምናሉ። እንደዚህ ዓይነት መለያየቶች እና የሰላም መደፍረስ አንዳንድ ጊዜ ጥሩ አስተዳደር ባለማግኘት ሊከሰት ይችላል። በዘመናችን ሁላችንም እንዳየነው በመገናኛ ብዙኃን እንደ ሰማነው በማኅበራዊ ትስስር ገጽ እንደ ተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን ያ ሁሉ መከራ ሲደርስባት፡ መከራ አድራሾቹ ላይ ጦርነት ከመክፈት ይልቅ ለሰላም ስትጠራቸው ነበር። እየተቃጠለችም እንኳን እጇን ለሰላም ዘርግታ ነበር። ይህ ለሰላም ምን ያህል ዋጋ እንደምትከፍል እና በሀገሪቱ ለሰላም እና ዕርቅ ያላትን ከፍተኛ ሚና የሚያሳይ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰላም ግንባታ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች። በዓለም ላይ ያሉ ሕዝቦች ፸፫ በመቶዎቹ በሃይማኖት ተጽእኖ ሥር እንደ ሆኑ እና በከፍተኛ ሁኔታ ከሃይማኖት ጋር ቁርኝት እንዳላቸው ይነገራል። (Rahel Alene Techane. The Role of the Two Dominant Religions, EOTC and Islam in Promoting Ethiopian Unit ፤ ራሄል አለነ ሁለቱ ተጽእኖ ፈጣሪ ሃይማኖቶች የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ እና እስልምና በኢትዮጵያ ሀገር አንድነት) በሚል ርእስ ለ፪ኛ ዲግሪ ማሟያ በሠራችው ጥናት ገጽ፩) ይህ ሃይማኖት የኅብረተሰብን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ተጽእኖ እንደሚያሳድርበት፣ ሃይማኖት ማኅበራዊ አንድነትን እንደሚያመጣ እና ሃይማኖት ለሰላም ግንባታ ትልቅ ሚና እንዳለው አመላካች ነው። ሃይማኖት ለሰው ልጆች ሁሉ ጥሩ እውነተኛነት እና በጎ የሆነ እሴት ያለው ነው። ሃይማኖት ዐመፅን፣ ጦርነትን አይሰብክም ከዚህ ይልቅ ሰላምን እና ኅብረተሰቡ በሰላም አብሮ መኖር እንዲችል የሚሰብክ ነው። በክርስትና ሃይማኖት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደቱ እስከ ዳግም ምጽአቱ የሰበከው ሰላምን ነው። ሲወለድ ቅዱሳን መላእክት ‹‹ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ›› ብለው ነበር የዘመሩት (ሉቃ. ፪፥፲፬)።

ስለ ጌታችንም ከነቢያት አንዱ ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹ሕፃን ተወልዶልናል፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፣ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል›› ብሎ ነግሮናል (ኢሳ. ፱፥፮) ጌታችንም በመዋዕለ ሥጋዌው በሕይወቱ ያሳየን በቃሉ የሰበከን ሰላምን ነው። ‹‹እኔ ሰላሜን እተውላችኋለው እኔ የምሰጣቹ ሰላም ዓለም እንደሚሰጣችሁ ዓይነት አይደለም›› በማለት (ዮሐ.፲፬፥፳፯) ሲነሣም ቅዱሳን ሐዋርያት በዝግ ቤት ሳሉ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ነው ያላቸው (ዮሐ. ፳፥፳)። ቅዱሳን ሐዋርያትም ይህንን ከጌታችን ያዩትን እና የተማሩትን አስተምረውናል ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ፲፪፥፲፰ ላይ ‹‹ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ›› በማለት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር እንደሚገባን አስተምሮናል።

ቤተ ክርስቲያን ከነቢያት ከጌታችን ከሐዋርያት በተማረችው ትምህርት መሠረት ዘወትር ስለ ሰላም ትማልዳለች። በቅዳሴያችን በእንተ ቅድሳት የተባለው የቅዳሴ ክፍል ላይ ‹‹ስለ ሰላም እንማልዳለን›› እንላለን፣ ካህኑ በቅዳሴ ወቅት ፲፪ ጊዜ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› በማለት ሰላምን ያውጃል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም ያላት ብዙ ነው፤ የተረበሸ ሁሉ ሰላም የሚያገኝባት ስፍራ ናት።

ሃይማኖታዊ ተቋማት ሃገራዊ ሰላም እና ልማት የማምጣት ሚናቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። የሃይማኖት አባቶች ሰላምን ለማምጣት ይቅር በማባባል የሚያደርጉት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። ዛሬ ዛሬ በሀገራችን በሃይማኖት፣ በቋንቋ እና በጎሳ ልዩነት ምክንያት የተፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎቻቸው የኢትዮጵያን አንድነት በማምጣት ረገድ የሃይማኖት ተቋማት ያላቸው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው።

የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ሀገራችን ኢትዮጵያ እንድትኖር ከሰላም ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም። ለችግሮቻችን ምንጩ ሰላም ማጣት ነው። ሰላም ለራሳችን፣ ለቤተሰባችን፣ ለጎረቤታችን፣ ለመንደራችን፣ ፤ ለአካባቢያችን እንዲሁም ለሀገራችን አስፈላጊ ነው።

## የሃይማኖት ተቋማት

የሃይማኖት ተቋማት የቆሙበት መሠረት ዓለማዊ አስተሳሰብ ባለ መሆኑ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ የሚኖሩ ምእመናን ሰላማዊውን መንገድ የሚናፍቁ በመሆናቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ የተበደሉ ወይም የበደሉ ወገኖች ካሉ በማስታረቅ፣ ያኮረፈ ወይንም የተገለለ ወገን ካለም የማስማማቱን ተግባር ይወጣሉ። የቆሙለት ዓላማም ከሀገር አልፎ በዓለም ላይ

ሰላምና ፍቅር እንዲሰፍን መጸለይና መትጋት ከሁሉም በፊት ቀድሞ የሚሠራ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያንም ሃይማኖት የሚሰበክባት ብቻ ሳትሆን ማኅበራዊ ጉዳይም የሚመለከታት ጭምር ናት፡፡ የራሷንም ሆነ የሀገሪቱን ችግር በሰላም ለመፍታት ትጥራለች፡፡ ተጠሪነትዋ ለክርስቶስ ቢሆንም የተሰየመችው ሕዝብን ልትመራ፣ ማኅበራዊ ተሳትፎ ልትፈጽም ጭምር ነው፡፡

ለዚህም ሰላምን በማስተማር ረገድ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ሚና አላት፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና የእውነተኛ ፍቅር ቤት ናትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰላምና ፍቅር እንዲሠፍን መቻቻል እንዲኖር በልዩ ልዩ መንገድ ስታስተምር የቆየች ሲሆን አሁንም በማስተማር ላይ ትገኛለች፡፡

## ዘላቂ ሰላም እንዴት መምጣት ይችላል?

ሰላም ማኅበራዊ ዕሴት ነው ሚዛናዊ የሆነ መስተጋብርን ይፈልጋል፡፡ የደካሞች ሰላም ሲከበር በማኅበረሰቡ ውስጥ የኃያላኑም ሰላም ይከበራል፡፡ ስለ ሰላም መምከር፣ አብዝቶ መሥራት፣ የሰላም መታጣት የሚያመጣውን ችግር በግልጽ ማስረዳት፣ ከደረሱብን የሰላም እጦት ሰው እንዲማርና ከሰላም ጎን አጥብቆ እንዲቆም ማድረግ ይገባል፡፡

**ከክርስትና እምነት አንጻር ሰላም ከእግዚአብሔር የመነጨና ከሰዎች ችሎታና ግንዛቤ በላይ የሆነ ጥሪ ነው፡፡ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ለዚህ ተልእኮ ይኖሩ ዘንድ ግዴታ አለባቸው፡፡**

ኦርቶዶክሳውያን ዓለምን ንቀው ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም እና ድኅነት ሲሉ እፍኝ ቆሎ እና ጥርኝ ውሃ እየቀመሱ ሌት ተቀን የሚጸልዩ አባቶች ስላሉን ወደ እነሱ ፊታችንን ልንመልስ ይገባናል፡፡ ሕዝብ ከሕዝብ ሲጋጭ ብሔራዊ መግባባት ሲጠፋ ሰላምን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና ምሕላን መያዝ ያስፈልገናል፡፡

ዘላቂ ሰላም መምጣት የሚችለው ወደ እግዚአብሔር ሰዎችን በማቅረብና ራስም በመቅረብ ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠንን ሰላም ሌላ ቦታ አናገኘውም፡፡ ይህ ሰላም ፍጹም ልዩ ነው፡፡ ‹‹አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል›› እንዲል፡፡ (ፊል. ፬፥፯) የሰው ልጅ በሃይማኖት ከኖረ ያለፈ በደልን በንስሓ አስተሥርዮ ከእግዚአብሔር ስለሚገናኝ ፍጹም ሰላምን ያገኛል፡፡

ዘላቂውን ሰላም ሰጪ ወደ ሆነው ልንቀርብ ይገባናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እርሱ ሰላማችን ነው›› (ኤፌ. ፪፥፲፬) እንዲል፡፡ ሰላም ሲጠፋ ተስፋ ሲጨልም ልብ ይታወካል፡፡ ነፍሳችን ሁሌ የምታርፍበት ወደብ ጌታችን ነው፡፡ አምላካችን የሚጠራን ለሰላም ነው፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ለሰላም ጠርቶናል›› (፩ቆሮ. ፯፥፲፭) በሰላም ተኝተን እንድናንቀላፋ ሰላምን ወደሚሰጠን አምላክ ሰላምን እንለምን፤ ‹‹በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁ አቤቱ አንተ ብቻህን በእምነት አሳድረኸኛል›› እንዲል (መዝ.፬፥፰)፡፡ የዛሬውንም ሆነ የነገውን ተስፋችንን ልናረጋግጥ የምንችለው ሰላም ሲሰፍን ነው፡፡

## ለሰላም መታጣት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ማንኛውም ዜጋ የሚፈልገውን አሳብ ለማራመድ ሰላም ያስፈልጋል፡፡ ከክርስትና እምነት አንጻር ሰላም ከእግዚአብሔር የመነጨና ከሰዎች ችሎታና ግንዛቤ በላይ የሆነ ጥሪ ነው፡፡ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ለዚህ ተልእኮ ይኖሩ ዘንድ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሰላም የሚታጣው የሰላምን ጥቅም ካለመረዳት፣ በሥጋዊ አስተሳሰብ መጠመድ፣ ነገን መርሳት፣

ፍቅር አልባነት፣ ጊዜያዊ ጥቅም፣ ድህነት፣ ሥራ ፈትነት እና መሰል ተግባራት ሲበዙ ነው።

በማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ የተለያዩ አንዳንዴም ተቃራኒ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ያልተጣጣሙ ፍላጎቶች የተነሣ የፖለቲካ ትግል ይፈጠራል። በዚህ ዓይነት የተፈጠረው የፖለቲካ ትግል የሚካሄደው ደግሞ አልፎ አልፎ ሕጋዊና ሞራላዊ በሆነ መልኩ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የማኅበረሰቡን ባሕል፣ ሕግ፣ እምነትና ግብረ ገብነትን በተቃረነ መንገድ ይሆናል።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ የቤተ ክርስቲያን ተግባርና ጉዳይ የልጆቿ አንድነት በሰላምና በኀብረት ተጠብቆ እንዲኖርና ከሁሉም ማኅበረሰብ ጋር ተስማምታ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ምእመናን አባላት የጋራ ጥረቶች ላይ ማሳተፍ ነው። ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም ታስተምራለች። ሰላም እንዲሆን ሰላም እንዲሠፍን ጥሪ ታቀርባለች፣ የምትሰብከው መጽሐፍ ቅዱሷም ቢሆን ሰላምን አጥብቆ ይሻል።

**ቤተ ክርስቲያን ከምንም በላይ የሀገር ሰላምና የሕዝቦች ደኅንነት ስለሚያሳስባት የጥላቻን ዘር በመዝራት የሚፈጸመውን አክራሪነት ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ጠንቅ መሆኑን ተረድታ ሰላምን ትሰብካለች። እንዲሁም የአክራሪነት አካሄድ ከሰው አልፎ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለሌለው ታወግዛለች።**

ቤተ ክርስቲያን ከሁሉ በላይ የምትፈልገው ደግሞ ውስጣችን በእምነትና በፍቅር አንድ እንዲሆን ነው። ይህን የውስጥ ወይም የመንፈስ አንድነትን የሚያጠናክር ትምህርቷም እንዲህ ይገለጻል። ‹‹ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ›› ይላል። (፩ቆሮ. ፩፥፲)።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ዕሴቷ (ኤፌ. ፩፥፳፫) ከላይ እንደተገለጸው ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ ከአምላኳ ከክርስቶስ ጋር ያላት አንድነት ነው። ሰብአዊ የሆነ ፍጡር ዘለዓለማዊ ድኅነትን ለማግኘት ሊመካበት የሚገባው ነገር ይህ ነው። ተለያዩ ሰዎች በፖለቲካ ልዩነትም ወይንም በሌሎች ጉዳዮች የተነሣ ቅራኔና በፖለቲካ ትግል ውስጥ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ልዩ ልዩ ፍላጎትና አመለካከት ያላቸው ሕዝቦች ወደ ሰላምና ትብብር እንዲመጡ ትሰብካለች ወይም ታስተምራለች።

## ሰላምን መረዳት አለብን

የሰው ልጅ ሰላምን መረዳት አለበት። ቤተ ክርስቲያን ከምንም በላይ የሀገር ሰላምና የሕዝቦች ደኅንነት ስለሚያሳስባት የጥላቻን ዘር በመዝራት የሚፈጸመውን አክራሪነት ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ጠንቅ መሆኑን ተረድታ ሰላምን ትሰብካለች። እንዲሁም የአክራሪነት አካሄድ ከሰው አልፎ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለሌለው ታወግዛለች። ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም ተነሥታ በዓለም የተስፋፋችው በጦር ኃይል ሳይሆን እውነተኛ በሆነው በወንጌል ትእዛዝ በመመራት ነው። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሲልካቸው አስገድዳችሁ ስበኩ አላለም። ሐዋርያትም ሆኑ ሊቃውንት ወደ ዓለም ሲሰማሩ ከአምላካቸው የተቀበሉትን የሰላም ወንጌል በመተግበር ነው።

## ሰላማዊ መሆን

ክርስቲያኖች የተጠሩት ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ነው። ሰላማዊነት የመንፈሳዊ ሰው አንዱ መገለጫው ነው። ሰላማዊ ሰው በማንኛውም በሚፈጸሙ ተግባራት

ፈጽሞ ልቡ አይርድም። የቱንም ያህል ችግር ቢደርስበት ሰላሙን አያጣም ነቢዩ ዳዊት ‹‹ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ›› (መዝ. ፳፮፥፫) እንዲል። አንድ ሰው ውስጣዊ ሰላሙን ካጣ ሁሉም ነገር በእርሱ እይታ የሚረብሸው፣ ትንሹም ነገር ውስብስብ ሊመስለው ይችላል። የልብ ሰላም ሲኖረን አእምሮአችንም ሰላም ይሰፍንበታል።

## ማጠቃለያ

ሰላም ስንል የተሟላ ሕይወት እንደ ሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ሌሎችን ማክበር በሰውነታቸውና በማንነታቸው ብቻ መቀበል፣ አካላዊ፣ መንፈሳዊና ሥነ ልቡናዊ ጦርነቶች አለመኖር፣ ፍትሐዊ የሆነ የሥልጣንና ሀብት ክፍፍል መኖርን፣ መቻቻልና ማኅበራዊነትን ይጠይቃል። በእንተ ቅድሳት በሚባለው የምልጃ ጸሎታችን ቀድመን የምንለምነው ልመናም ከሁሉ አስቀድሞ በክርስቶስ ሥጋ እና ደም ስለሚጸናው መንፈሳዊ አንድነት ሰላም መሆን ልመናን እናቀርባለን። "አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን" ይላል። የቅድስት ማኅበር አባላት ስለ ሆኑት ስለ ሐዋርያት፣ ስለ ሰማዕታት፣ ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ፣ ስለ ሊቀ ጳጳሱ፣ ስለ ቀሳውስት… እያልን ከመጸለያችን በፊት ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እግዚአብሔርን እንለምነዋለን።

የእግዚአብሔር መንገድ ጽድቅ፣ ፍቅር፣ ሰላም በአጠቃላይ በጎ ሥራን ሁሉ መሥራት ነው። የቅድስና ሕይወት ማለት በቅድስና መመላለስ ማለት ነው። የቅድስና ሕይወት የሰላምን ሕይወት በሚመሩ መካከል ያለ ሀብት ነው።

ሰላምን መከተል ተግባራዊ የሆነ የቅድስናን ኑሮ በክርስቶስ ሆኖ ከመምራት ውጭ ምን ሆኖ ሊታሰብ ይችላል? እርሱ ሰውን ወዳጅና የሰላም ንጉሥ ነው። ዓለም ቢሸሹት ይከተላል። ቢከተሉት ገደል ይሰዳል። በዓለም ውስጥ ስንኖር አኗኗራችን እንደ ዓሣ ምግብ በብልሃት ማድረግ ያስፈልጋል። የዓለም ክፋት ትዝ እያለን ወደ ዓለም የምንመለስ ከሆነ በኀጢአቷ ታጠምደናለች በዓለም ውስጥ እየኖርን ግን ዓለምን ስንርቅ በቅድስና ሕይወት መኖር ይቻለናል። አበው ‹‹በእባብ ማሳት ምክንያት በበደልን ጊዜ ከዘለዓለማዊ ሕይወት ራቅን ደስታ ካለባት ከገነትም ወጣን አንተ ግን ለዘለዓለሙ አልጣልኸንም፤ በቅዱሳን ነቢያትህ ጎበኘኸን እንጂ በኋላ ዘመንም በጨለማና በሞት ጥላ ለምንኖር ለእኛ ታየህልን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በእጅ ላይ አበራህ።›› (ቅዳሴ ዘባስልዮስ) እያሉ አጥተነው የነበረውን የቅድስና ሕይወት እንዴት እንደተመለሰልን ይገልጻሉ።

✟ ✟ ✟